
# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

### የተማሪ መጽሐፍ




## 5ኛ ክፍል

# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 5ኛ ክፍል


**አዘጋጆች**

ትንሳኤ ጀምበሬ

ንጉሴ ዴአታ

**አርታኢ**

ግርማ በቀለ

**የጥራት ተቆጣጣሪዎች**

ይልፋሸዋ ጥላሁን

በርናባስ ደበሎ

ታምሩ ገለታ

**ግራፊክስ እና ምስል ገለፃ**

ሰለሞን አለማየሁ ጉተማ

© የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ 2014 ዓ.ም.

ይህ መፅሐፍ በ2014 ዓ.ም. በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በነቀምቴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በትብብር የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2014 ዓ.ም. የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ነው። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም።

የቅጂ መብቶችን ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

# ማውጫ

መቅድም ........ iv

መግቢያ ........ v

ምዕራፍ አንድ፡ ጓደኝነት ........ 1

ምዕራፍ ሁለት፡ ንፅህናና ፅዱነት ........ 17

ምዕራፍ ሶስት፡ ትውፊት ........ 32

ምዕራፍ አራት፡ የመንገድ ደህንነት ........ 43

ምዕራፍ አምስት፡ አካባቢ ጥበቃ ........ 58

ምዕራፍ ስድስት፡ አደንዛዥ ዕጾችና ንጥረነገሮች ........ 73

ምዕራፍ ሰባት፡ ምግብ ........ 87

ምዕራፍ ስምንት፡ የዱር እንስሳት ........ 104

ምዕራፍ ዘጠኝ፡ ባህላዊ ጨዋታዎች ........ 119

ምዕራፍ አስር፡ ስነቃል ........ 135

# መቅድም

ትምህርት ሚኒስቴር "ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለውን ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ" በሚል ትኩረት በመስጠት አዲስ ሥርዓተትምህርት ቀርጾ አቅርቧል። በዚህ መሠረት በሥርዓተትምህርቱ ታይቶ የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ምርምር ተደርጓል። ከምርምሩ የተገኙ አቅጣጫዎችም የተማሪዎቹን ደረጃ አለመመጠን፣ የትምህርቱ አንኳር ጽንሰሀሳቦች ግልጽ አለመሆን፣ ከይዘቱ መታጨቅ የተነሳ ለዓመቱ ከተመደበለት ክፍለጊዜ ጋር አለመመጣጠን እና ከተጓዳኝ ሥርዓተትምህርቶች አማራጭ ግብዓቶችን አለመጠቀም ናቸው። ስለሆነም የአፍመፍቻ ቋንቋ ልህቀትን ለማሻሻል፣ በአውድ የተደገፈ ለማድረግ እና በመማር ላይ የተመሰረተ የመማር ስኬታማነትን ለማረጋገጥ ተቀርጿል።

ሥርዓተትምህርቱን መሠረት በማድረግ የትምህርት መሣሪያዎች ተዘጋጅተዋል። ከእነዚህም ውስጥ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ አንዱ በመሆኑ ይህ አማርኛ እንደአፍመፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ሊዘጋጅ ችሏል። መጽሐፉም ተማሪዎች ቢያንስ መጎናጸፍ ያለባቸውን ብቃት (Minimum Learning Competency)፣ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶችን፣ ተግባቦታዊ የመማር ዘዴን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው።

ከዚህ አንፃር የዚህ መጽሐፍ ዝግጅት በቀድሞው የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ የተስተዋሉ ክፍተቶችን ይሞላል ተብሎ ይጠበቃል።

## መግቢያ

ይህ መማሪያ መጽሐፍ አስር ምዕራፎች አሉት። እያንዳንዱ ምዕራፍ ደግሞ በስሩ ስድስት ንዑስ የትምህርት ክፍሎችን አካቷል። እነዚህም ትምህርት አንድ ማዳመጥ፣ ትምህርት ሁለት መናገር፣ ትምህርት ሶስት ማንበብ፣ ትምህርት አራት መጻፍ፣ ትምህርት አምስት ቃላት እና ትምህርት ስድስት ሰዋስው ናቸው። እያንዳንዱ የትምህርት ክፍል በመርሃትምህርቱ በተደለደለው መሰረት በክፍለጊዜ ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን በስሩ መመሪያዎች፣ ትዕዛዞች፣ መልመጃዎች እና ተግባሮች አካቷል። ከዚህ አኳያ የቋንቋ ክሂሎች የተደራጁት በቅድመተግባር፣ በጊዜተግባር እና በድህረተግባር ሂደታዊ አቀራረብ ነው። የቋንቋ የዕውቀት ዘርፎች ደግሞ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ማቅረቢያ ዘዴን ተከትለዋል። በዚህ መሰረት የመማሪያ መጽሐፉ ማስተማሪያ ዘዴ ተማሪ ተኮር እንዲሆን ተደርጓል።

# ምዕራፍ አንድ፡ ጓደኝነት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ስለጓደኝነት ያዳመጣችሁትን በተመለከተ አድናቆታችሁን ትገልፃላችሁ፤
- የቀረበላችሁን ፅሑፍ በማንበብ ዋናውን ሃሳብ ትገልፃላችሁ፤
- ስለጓደኞቻችሁና ስላሳለፋችሁት ጊዜ ቀለል ያሉ አረፍተ ነገሮችን በመጠቀም አንቀፅ ትፅፋላችሁ፤
- ያነበባችሁትን ምንባብ መሠረት በማድረግ ተዛማጅ ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፤
- የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍችዎች ትናገራላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ሥር "አዶዬ" በሚል ርእስ ጽሁፍ እና መልመጃ ቀርቦላችኋል። ስለሆነም በትኩረት አዳምጣችሁ በስሩ የቀረበውን መልመጃ ትሰራላችሁ።

### አዶዬ

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

**ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ከዚህ በፊት ስለ "አዶዬ" የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. "አዶዬ" የሚባሉት እነማን እንደሆኑ ግምታችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ጽሁፉን እያዳመጣችሁ አዳዲስ ቃላትን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ።
2. ጓደኛን ለመምረጥ እንደመስፈርት የሚያገለግሉት ምን ምን እንደሆኑ በማስታወሻ ደብተራችሁ ጻፉ።

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ቀደም ሲል መምህራችሁ ያነበቡላችሁን በማስታወስ ተከታዮቹን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ካዳመጣችሁት ጽሁፍ ያስደነቃችሁን ነገር ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. አንድ ሰው ከሁሉም ጋር ጓደኛ መሆን የማይችለው ለምን ይመስላችኋል?
3. “አዶዬ! አዶዬ! አቤት! ስምሽን ዳግም ብጠራው ስሜን ሞት ይጥራው፤ የኔንም ሞት ይጥራው” የሚባባሉት ለምንድን ነው?

4. "የአዶዬን" የቃለመሃላ ሥርዓት አፈፃፀም በቅደም ተከተል አስረዱ።
5. "አዶዬዎች" የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ዘርዝሩ።

**ለ. ከሚከተሉት ሀሳቦች መካከል ትክክል የሆኑትን “እውነት” ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ “ሀሰት” በማለት መልሱ።**

1. ከሁሉም ሰው ጋር ጓደኝነት መፍጠር ይቻላል።
2. ጓደኝነት ከሚፈጠርበት አንዱ አብሮ በመማር ነው።
3. ልጃገረዶች ለአዶዬነት የሚመራረጡት በቤተሰብ ምርጫ ነው።
4. አዶዬዎች በደስታም ሆነ በሀዘን ጊዜ አይለያዩም።
5. **“የእጮኛ መስፈርት...”** ሲል ለጋብቻ ከሚጠይቀው ሰው የሚጠበቁ ነገሮች ማለት ነው።

**ክፍለጊዜ ሶስት**

## ትምህርት ሁለት፡መናገር

በዚህ ትምህርት ክፍል የመናገር ክሂላችሁን እንድታዳብሩ የሚያግዙ ተግባሮች ቀርበዋል። ስለሆነም ተግባሮቹን በተሰጡት ትዕዛዞች መሰረት ስሩ።

**ተግባር አንድ**

1. ከትምህርት ሰዓት ውጭ ከጓደኞቻችሁ ጋር የዕረፍት ቀናችሁን ምን በማድረግ እንደምታሳልፉ ለክፍል ተማሪዎች ተናገሩ።

2. ጓደኞቻችሁ የዕረፍት ጊዜያቸውን በማይረባ ነገር ሲያጠፉ ብትመለከቷቸው ምን ብላችሁ እንደምትመክሯቸው በቡድን ተወያይታችሁበት በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

**ክፍለጊዜ አራት**

**ተግባር ሁለት**

ሰዎች ትርፍ ጊዜያቸውን እንዴት እንደሚጠቀሙበት ጠይቃችሁ የሚነግሯችሁን ማስታወሻ በመያዝ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

**ክፍለጊዜ አምስት**

**ተግባር ሶስት**

ከታች ባሉት መነሻ ሃሳቦች መሰረት ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ የርስ በርስ ትውውቅ አድርጉ። የትውውቅ ተግባሩንም ተራ በተራ ወደፊት እየወጣችሁ በክፍል ውስጥ ለመምህራችሁ አሳዩ። በትውውቅ ወቅት ሙሉ ስማችሁን፣ የምትማሩበትን ትምህርት ቤትና የክፍል ደረጃ፣ የምትኖሩበትን ሰፈር እና የመሳሰሉትን ጥቀሱ።

**ክፍለጊዜ ስድስት**

**ተግባር አራት**

መምህራችሁ የሰላምታን አጠቃቀም ከጊዜ አንፃር በመከፋፈል ምን ምን እንደሚባል ይነግሯችኋል። እናንተም መምህራችሁ የሚሉትን ተከትላችሁ ደግማችሁ ተናገሩ።

ክፍለጊዜ ሰባት

# ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ሥር ምንባብ ቀርቦላችኋል። ምንባቡን እያነበባችሁ የአንቀጾቹን ዋና ዋና ሀሳቦች ማስታወሻ ትይዛላችሁ። ከዚያም ከምንባቡ ለወጡ የተለያዩ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ትሰጣላችሁ።



## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

1. ጓደኝነት የሚመሰረትባቸው አጋጣሚዎች ምን ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ገምቱ።
2. እናንተም ጓደኛ ያገኛችሁት የት እና በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሆነ ግለፁ።

## ጓደኝነት

ጓደኝነት የሚከሰትባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው። ከነዚህም ውስጥ አንዱ በአንድ አካባቢ መወለድና አብሮ ማደግ ነው። ይህ ጓደኝነት ከልጅነት እስከ ሽምግልና ዕድሜ አብሮ የሚዘልቅ ሊሆን

ይችላል። ሌላው በዕድሜ **አቻነትና** በፆታ ተመሳሳይነት የሚፈጠር ጓደኝነትም አለ። በተጨማሪም በትምህርት ዓለም **ግንኙነት** ጓደኝነት ሊመሰረት ይችላል። እንዲሁም ተመሳሳይ ፍላጎትና አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ጓደኝነት የሚመሠርቱበት ዕድል ይኖራል። እንግዲህ እነዚህ አጋጣሚዎች **ለአብነት** የቀረቡ ይሁኑ እንጂ ሌሎችም እንዳሉ መገንዘብ ያስፈልጋል ።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

| |
|---|
| ቀደም ሲል ጓደኝነት ስለሚመሰረትባቸው አጋጣሚዎች የገመታችሁት እና አንቀፁን ካነበባችሁ በኋላ የተረዳችሁት ሃሳብ ተቀራራቢነት አለው ትላላችሁ? እንዴት? |

አንድ ሰው በህይወት ዘመኑ ጓደኛ እንዲኖረው ይመከራል። ምክንያቱም በችግር ጊዜም ይሁን በደስታ ጊዜ ሐሳቡን የሚያካፍለው ጓደኛ ያስፈልገዋል። በተጨማሪም በአንድ ጉዳይ ላይ ምክር መጠየቅ ቢያስፈልገው ጓደኛ የሚኖረው **ድርሻ** ቀላል አይደለም። የጓደኛ አስፈላጊነት በዚህ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ሌላም ጥቅም አለው። ለምሳሌ እርስ በርስ ለመማማር የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ይህም አንዱ የሚያውቀውን ነገር ሌላው ላያውቀው ስለሚችል ነው።

በእርግጥ አንዳንድ ሰዎች "ለኔ ሰው አይወጣልኝም" ሲሉ ይደመጣሉ። ብዙ ሰዎች ግን አባባሉ የግለሰቡን ድክመት የሚያሳይ እንደሆነ ያምናሉ። ምንም እንኳን ሁሉም ሰው የራሱ **ጠባይ** ያለው መሆኑ ቢታወቅም ሰው ከጓደኛው ጋር አብሮ

ለመኖር ሲል ራሱን የሚለውጥበት አጋጣሚ አለ። ይህም ጓደኛው የወደደውን አብሮ በመውደድ፣ የጠላውን ደግሞ አብሮ በመጥላት የሚገለፅ ነው። እዚህ ላይ ሰው ለጓደኛው ሲል እራሱን የሚለውጠው እስከምን ድረስ ነው? ልንል እንችላለን። ይህም የሚሆነው ጓደኛዬ የምንለው ሰው በግል ባለን ኑሮ ላይ **ተፅዕኖ** እስካላስከተለ ድረስ ነው። ነገር ግን ከትክክለኛው መስመር የሚያስወጣ መንገድ የሚከተል ከሆነ **በቸልታ** ዝም ብሎ ማለፍ አይገባም። በተቻለ መጠን ጓደኛን ከስህተት **መንገድ** ለመመለስ **ወዲያውኑ** መምከር ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል አንዳንድ ሰዎች በጓደኝነት ሰበብ ለጥቅም ሲሉ ሰውን የሚቀርቡ አሉ። እነዚህ ሰዎች የጓደኝነት ፍቅር ሳይኖራቸው የግል ፍላጎታቸውን ለማሟላት ብቻ ጓደኝነትን የሚመሰርቱ ናቸው። ጥቅም ፈላጊ ሰዎችም በመሆናቸው የሚያሳዩዋቸው ባህርያት አሏቸው። እነዚህ ሰዎች በደስታ ጊዜ ካልሆነ በችግር ጊዜ የሚሸሹ ናቸው። የሚፈልጉትን ነገር ካላገኙም ችግር ባለበት ቦታ ሁሉ የሚገኙ አይደሉም። ይህ ደግሞ **ራስ ወዳድ** መሆናቸውን የሚያሳይ ነው። ስለዚህ በተቻለ መጠን ትክክለኛ የሆነ ጓደኛ እንዲኖረን አስቀድመን መምረጥ ያስፈልጋል።

(ከአፋን ኦሮሞ የመማሪያ መጽሐፍ 8ኛ ክፍል ካለው ተተርጉሞና ለክፍል ደረጃው በሚመጥን ተሻሽሎ የቀረበ)

ክፍለጊዜ ስምንት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. አንድ ሰው በህይወት ዘመኑ ጓደኛ እንዲኖረው የሚመከረው ለምን እንደሆነ ግለፁ።
2. ጥቅም ፈላጊ ሰዎች የተባሉት ምን ዓይነት ባህርይ አላቸው?
3. በአንቀጽ አንድ የተጠቀሰው ዋና ሀሳብ ምንድን ነው?
4. የጓደኝነት ፍቅር ስለሌላቸው ሰዎች የተገለፀው በየትኛው አንቀፅ ነው?
5. ጓደኝነት ስለሚመሰረትባቸው አጋጣሚዎች ሃሳብ የተገለፀው በየትኛው አንቀፅ ነው?
6. ከጓደኛ ጋር አብሮ ስለመኖር ሃሳብ የቀረበው በየትኛው አንቀፅ ነው?
7. የፅሑፉ ዋና ሃሳብ ምን እንደሆነ ግለፁ።

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

### መልመጃ ሶስት

ለ. ከሚከተሉት ሀሳቦች መካከል ትክክል የሆኑትን “እውነት” ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ “ሀሰት” በማለት ከመለሳችሁ በኋላ መልሳችሁን በምክንያት አስደግፉ።

1. እውነተኛ ጓደኛ እንዳለ ሁሉ ጥቅም ፈላጊ ጓደኛም አለ።

2. አንድ ሰው ጓደኛ የሚያስፈልገው ችግር ሲያጋጥመው ብቻ ነው።
3. በጓደኞች መካከል የሚደረግ መቀራረብ እርስ በርስ ለመማማር እድል ይፈጥራል።
4. አብሮ አደግ ጓደኞች ከልጅነት እስከ ሽምግልና ዕድሜ አብረው ሊኖሩ ይችላሉ።
5. "ለኔ ሰው አይወጣልኝም" የሚሉ ሰዎች ሃሳባቸው በብዙ ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት አለው።
6. ራስ ወዳድ የሆነ ሰው ጓደኛው ችግር ሲያጋጥመው ቀድሞ በቦታው የሚገኝ ነው ።

**ተግባር አምስት**

ጓደኝነት ከሚመሰረትባቸው አጋጣሚዎች በፅሑፉ ውስጥ ከተጠቀሱት ውጪ ሌሎች አጋጣሚዎች ካሉ ጥቀሱ።

**ክፍለጊዜ አስር**

## መልመጃ አራት

**ሐ. በምድብ "ሀ" ስር ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳያቸውን ከምድብ "ለ" በመምረጥ አዛምዱ።**

| " ሀ " | " ለ " |
|---|---|
| 1. አቻነት | ሀ. አቅጣጫ |
| 2. ራስ ወዳድ | ለ. ጫና |
| 3. መስመር | ሐ. ቆይቶ |
| 4. ቸልታ | መ. በፍጥነት |

5. ተፅዕኖ ሠ. እኩልነት
6. ወዲያውኑ ረ. ምንቸገረኝነት
7. አብነት ሰ. እድል
8. ድርሻ ሸ. ለሌሎች የማያስብ
9. ግንኙነት ቀ. አመል
10. ጠባይ በ. ምሳሌ
ተ. አፍቃሪ
ቸ. ቀረቤታ

መ. በምድብ "ሀ" ሥር ከምንባቡ ለተገኙ ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከምድብ "ለ" በመምረጥ አዛምዱ።

| " ሀ " | " ለ " |
| --- | --- |
| 1. ብዙ | ሀ. መውደድ |
| 2. ጥቅም | ለ. ከባድ |
| 3. ከፍተኛ | ሐ. ጥንካሬ |
| 4. ቀላል | መ. ማጓደል |
| 5. ደስታ | ሠ. ጥቂት |
| 6. መጥላት | ረ. መቅረብ |
| 7. ድክመት | ሰ. በርካታ |
| 8. ፍቅር | ሸ. ጥላቻ |
| 9. ማሟላት | ቀ. ጉዳት |
| 10. መሸሽ | በ. መራቅ |
| | ተ. ዝቅተኛ |
| | ቸ. ሀዘን |

ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## ትምህርት አራት፡ መፃፍ

በዚህ ትምህርት ሥር አንቀፅ ትፅፋላችሁ፤ በአንቀፅ ውስጥ የሚገኙ ዓረፍተነገሮችን ትለያላችሁ፤ በተጨማሪም የውሎ ማስታወሻ ትፅፋላችሁ።

### ማስታወሻ

**አንቀፅ**

አንቀፅ ማለት አንድን ነጠላ ሃሳብ ብቻ የሚገልፅ የፅሁፍ ክፍል ነው። አንቀፅ በአረፍተነገሮች የሚዋቀር፣ ዓላማ ያለው ነው።

**በአንቀፅ ውስጥ የሚገኙ ዓረፍተነገሮች**

አንቀፅ በውስጡ ሁለት ዓይነት ዓረፍተነገሮች ይይዛል። እነሱም ሀይለቃልና ዘርዛሪ ዓረፍተነገሮች ናቸው።

ሀይለቃል የሚባለው የአንቀፁን ዋና ሃሳብ የያዘው ዓረፍተነገር ነው። ዘርዛሪ ዓረፍተነገሮች በአንቀፅ ውስጥ ያለውን ሀይለቃል የሚያብራሩ ዓረፍተነገሮች ናቸው።

**ምሳሌ**

**ወተት በተፈጥሮው የተለያዩ ንጥረ ነገሮችን ያካተተ ምግብ ነው። ወተት ሀይልና ሙቀት የሚሰጥ፣ አካልን የሚገነባ፣ በሽታን የሚከላከል ንጥረነገሮች አለው። በተጨማሪም ቅባት፣ ማዕድንና ውኃን አካቶ ይዟል።**

ከላይ በቀረበው አንቀጽ ውስጥ ደምቆ የተጻፈው የመጀመሪያው ዓረፍተነገር ሀይለቃል ሲሆን፣ ሌሎቹ ደግሞ ዘርዛሪ ዓረፍተነገሮች ናቸው።

## ተግባር አምስት

ከዚህ በላይ ያለውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ በትምህርት ቤት ውስጥ ከጓደኞቻችሁ ጋር ጊዜያችሁን እንዴት እንደምታሳልፉ የሚገልፅ አንድ አንቀጽ ጻፉ።

### ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ተግባር ስድስት

ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ አንብባችሁ ሀይለቃልና ዘርዛሪ ዓረፍተነገሮች ያሉት አንድ አንቀፅ ፃፉ።

### ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

ቀጥሎ በአንድ አንቀፅ የተዋቀረውን የአንድ ቀን የውሎ ማስታወሻ ምሳሌ ተመልከቱ። ከዚያም ከመምህራችሁ የሚሰጣችሁን ገለፃ በደንብ ተከታተሉና ማስታወሻችሁ ላይ መዝግቡ።

## የውሎ ማስታወሻ

ዛሬ ጠዋት ከመኝታዬ ተነስቼ አልጋዬን ካነጠፍኩ በኋላ ወደ መፀዳጃ ቤት ሄድኩ። ከዚያም ፊቴን ታጥቤ፣ ፀጉሬን አበጥሬ የተዘጋጀልኝን ቁርስ በልቼ ወደ ትምህርት ቤት አመራሁ።

ትምህርት ቤቴ ከደረስኩ በኋላ ዘወትር እንደማደርገው የሰንደቅ ዓላማ ስነስርዓት አክብሬ ወደ ክፍሌ ገባሁ። በክፍል መምህሬ ስም ከተጠራሁ በኋላ የመጀመሪያዎቹን ሶስት ክፍለጊዜያት ተምሬ ሲደወል ለዕረፍት ወጣሁ። በዕረፍት ሰዓት እናቴ በሰጠችኝ ገንዘብ ከትምህርት ቤታችን ክበብ ሻይ ገዝቼ ጠጣሁ። የዕረፍት ሰዓት በመጠናቀቁ ወደ ክፍሌ ተመለስኩና ቀሪዎቹን ሶስት ክፍለ ጊዜያት ተማርኩ። በመጨረሻም የስድስተኛው ክፍለጊዜ ማብቂያ ደወል በመደወሉ ከክፍሌ ወጥቼ ወደ ቤቴ ሄድኩ።

(አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ የተማሪ መጽሐፍ 7ኛ ክፍል፣ ተሻሽሎ የቀረበ)

ክፍለጊዜ አስራ አራት

### ተግባር ሰባት

በአንድ ሳምንት ውስጥ ያከናወናችሁትን የየዕለት ዋና ዋና ተግባሮችን የሚገልፅ የውሎ ማስታወሻ ፅፋችሁ አቅርቡ።

ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ክፍል ለቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ትፈልጋላችሁ፤ እንዲሁም ስዕላዊ መግለጫዎችን ከቃላት ጋር ታዛምዳላችሁ።

### ተግባር ስምንት

**መዝገበቃላት በመጠቀም ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ቀጥተኛ ፍቻቸውን ፃፉ።**

1. አጋጣሚ
2. ዘወትር
3. ሰበብ


4. ባህርይ 5. መለወጥ

የቃላት ቀጥተኛ ፍች የመዝገበቃላት ፍች ነው።

**ክፍለጊዜ አስራ ስድስት**

## መልመጃ አምስት

የሚከተሉትን የስፖርት ስዕላዊ መግለጫዎች ምንነት ከሚገልፁ ቃላት ጋር በመስመር እንዲገናኙ በማድረግ አዛምዱ።




## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ሥር የወል እና የተፀውዖ ስሞችን ትለያላችሁ፤ በተጨማሪም ትፅፋላችሁ።

ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

## ተግባር ዘጠኝ

### ማስታወሻ

**የወል እና የተፀውዖ ስሞች**

የወል ስም የምንለው አንድ ዓይነት የሆኑ ነገሮች በጋራ የሚጠሩበት ስም ነው።

ለምሳሌ ፡ መምህር፣ ሀኪም፣ ተማሪ፣ ፖሊስ፣ በግ፣ ወንዝ፣ መኪና፣ ነብር፣ ወዘተ.

የተፀውዖ ስም የምንለው አንድ ነገር ለብቻው ተለይቶ የሚታወቅበት የግል መጠሪያ ስም ነው።

የሰው ስም፡ መገርሳ፣ ቦንቱ፣ ከድር፣ ፋጡማ

የሀገር ስም፡ ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ሱዳን፣ ጂቡቲ

የከተማ/የቦታስም፡ አዳማ፣ መቱ፣ ነቀምቴ፣ አምቦ፣

የወንዝ ስም፡ አዋሽ፣ አባይ፣ ጊቤ፣ ዳቡስ

የሐይቅ ስም፡ ወንጪ፣ ደምበል፣ ሀዋሳ፣ ጣና

**ሀ. ቀጥሎ በተሰጣችሁ ምሳሌ መሠረት የምታውቋቸውን የቤት እና የዱር እንስሳትን የወል ስሞች ዘርዝሩ።**

ምሳሌ፡

| የቤት እንስሳት | የዱር እንስሳት |
|---|---|
| ውሻ | ቀበሮ |

**ለ. ከላይ ከዘረዘራችኋቸው የቤት እና የዱር እንስሳት መካከል**

**አራት አራት የእንስሳት ስሞችን መርጣችሁ ከታች ባለው ምሳሌ መሰረት ዓረፍተነገሮች መስርቱባቸው።**

ምሳሌ፡

1. ውሻ ታማኝ የቤት እንስሳ ነው።
2. ቀበሮ የዱር እንስሳ ነው።

**ክፍለጊዜ አስራ ስምንት**

## ተግባር አስር

ሐ. በሠንጠረዡ ውስጥ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት የምታውቋቸውን የሰው፣ የወንዝ፣ የሐይቅ፣ የከተማ/የቦታ ስሞችን ዘርዝሩ። ለእያንዳንዱ የስም ዓይነት አምስት አምስት የተፀውኦ ስሞችን መዘርዘር ይጠበቅባችኋል።

| የሰው ስም | የወንዝ ስም | የሐይቅ ስም | የከተማ/የቦታ ስም |
|---|---|---|---|
| ሞሚና | ዋቢ ሸበሌ | ላንጋኖ | ጂማ |

መ. ከዚህ በታች የተለያዩ ስሞች ተዘርዝረዋል ። ከነዚህም ውስጥ የወል ስም የሆነውን "የወል ስም" የተፀውዖ የሆነውን ደግሞ "የተፀውዖ ስም" እያላችሁ ከጎናቸው ፃፉ።

1.ግመል
2.ገበሬ
3.ወታደር
4.ሮቤ
5.ገመቹ
6.ቢሾፍቱ
7.መኪና
8.አንበሳ
9.ጭላሎ
10.ጅብ
11.ዜይነባ
12. ራስ ዳሽን

# ምዕራፍ ሁለት፡ ንፅህናና ፅዱነት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ከምንባቦች የወጡ ጥያቄዎችን አዳምጣችሁ ትመልሳላችሁ፤
- ፅዳትን በተመለከተ ሰዎች የሚያከናውኑትን ትናገራላችሁ፤
- በክፍል ደረጃው ትክክለኛውን ንባብ ትለማመዳላችሁ፤
- ተገቢ ርዕስን በመጠቀም አጭር አንቀፅ ትፅፋላችሁ፤
- የይዘትና አዳዲስ ቃላትን ትተዋወቃላችሁ/ ትወያያላችሁ፤
- የቀለም መዋቅርንና ምዕላድን ትረዳላችሁ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ሥር አዳምጣችሁ እንድትረዱ የሚያግዟችሁ ጽሁፍ እና መልመጃ ቀርቦላችኋል። በዚህ መሰረት የተለያዩ የግንዛቤ ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ።

ክፍለጊዜ አንድ

### የእነአረጋ መማሪያ ክፍል



### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ከምስሉ የተገነዘባችሁትን ተናገሩ።
2. በቀጣይ ስለምን የምታዳምጡ ይመስላችኋል?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

እያዳመጣችሁ ክፍት ቦታዎችን አሟሉ።

1. እነአረጋ ክፍላቸውን በ_____ ያጸዳሉ።
2. የሰበሰቡትን ቆሻሻዎች በ_____ ያጠራቅማሉ።
3. አረጋ እና ጓደኞቹ የክፍላቸውን ጠረጴዛ እና ወንበሮችን በቁርጥራጭ_____ እና በውሃ ያጸዳሉ።

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድናችሁ በመወያየት የተስማማችሁበትን መልስ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።**

1. እነአረጋ የመማሪያ ክፍላቸውን ለምን ሁልጊዜ ያጸዳሉ?
2. ክፍላቸውን ሁልጊዜ በማጽዳታቸው ምን ተጠቀሙ?

**ተግባር አንድ**

ጥንድ ጥንድ በመሆን ቤታችሁን እና አካባቢያችሁን እንዴት እንደምታጸዱ ሀሳብ ተለዋውጣችሁ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍል ተማሪዎች በቃል አቅርቡ።

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ሥር ሰዎች ቆሻሻ በሚያስወግዱበትና ንፅህና በሚጠብቁበት ሁኔታ ላይ ሀሳብ ትለዋወጣላችሁ። እንዲሁም ትወያያላችሁ።

**ክፍለጊዜ ሶስት**

**ተግባር ሁለት**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ በቡድናችሁ ተወያዩባቸው።

1. ፕላስቲክ ነክ ቆሻሻዎችን ያለአግባብ ማስወገድ በአካባቢ ላይ የሚያደርሰው አሉታዊ ተጽእኖ
2. በወንዞች አካባቢ ቆሻሻ መጣል የሚያስከትለው ጉዳቶች

**ክፍለጊዜ አራት**

**ተግባር ሦስት**

ሰዎች ቆሻሻ በሚያስወግዱበት ጊዜ ማድረግ ስለሚገባቸው ነገር በቡድን ተወያይታችሁ የተስማማችሁበትን ሃሳብ በተወካያችሁ አማካይነት ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

**ተግባር አራት**

**ክፍለጊዜ አምስት**

ሰዎች በአካባቢያችሁ ፅዳትን ለመጠበቅ ምን ምን ተግባሮችን እንደሚያከናውኑ በመጠየቅ ያገኛችሁትን ምላሽ በዘገባ መልክ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አምጥታችሁ ተናገሩ።

ተግባር አምስት

ክፍለጊዜ ስድስት

ቀጥሎ ጥንድ በመሆን የአካባቢ ንጽህናን በተመለከተ አንዳችሁ በምልክት ሌላኛችሁ ደግሞ የምልክቱን መልዕክት በቃል አስረዱ። በዚህ መሰረት ሌሎቻችሁም ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ ተጠያየቁ። ለአንድ ቡድን የተፈቀደው አንድ ጥያቄ ብቻ ነው።

ምሳሌ፡ ፊት መታጠብን በምልክት ወይም በእንቅስቃሴ ማሳየት ሊሆን ይችላል።

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ክፍል የቀረበውን ምንባብ አቀላጥፋችሁ በየግላችሁ በማንበብ ዋና ዋና ሃሳቦችን ትመዘግባላችሁ። ከዚያም መልመጃዎችንና ተግባሮችን ትሠራላችሁ።

ክፍለጊዜ ሰባት

### የቅድመንባብ ጥያቄዎች

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመወያየት ተገቢ የሆነ መልስ በቃል ስጡ።

1. በሀገራችን በተለምዶ በአመት አንድ ጊዜ በየሰፈሩ ቆሻሻን ሰብስቦ የማቃጠል ተግባር ምን እንደሚባል የምታውቁትን ግለፁ?
2. ሰዎች ይህን ቆሻሻ ሰብስቦ የማቃጠል ተግባር የሚፈፅሙት ለምን ይመስላችኋል?

# "ህዳር ሲታጠን"



በሀገራችን በተለምዶ ህዳር ሲታጠን በሚል በየዓመቱ በወርሃ ህዳር የሚከናወን ቆሻሻን ሰብስቦ የማቃጠል ልማድ አለ። ይህ ተግባር ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፈ የመጣ ነው። የህዳር ሲታጠን አመጣጥ ታሪክ የራሱ መላምት አለው። ይህም በ16ኛው ክፍለ ዘመን ተከስቶ ከአውሮፓ ተነስቶ እስከ አፍሪካ የዘለቀውና "ስፓንሽ ፍሉ" የሚባለውን ወረርሽኝ ለመከላከል የተደረገውን እንቅስቃሴ የሚመለከት ነው። በወቅቱ መላ ህዝቡ በአካባቢው የሚገኝን ቆሻሻ በማቃጠል የራሱንና የእንስሳቱን ህይወት የታደገበት መሆኑ ይገለፃል። ይህ ደግሞ ህዝቡ ቆሻሻን በማቃጠል የአካባቢውን ፅዳት መጠበቅና ራሱን ከበሽታዎች መከላከል የጀመረበት ጊዜ የቆየ መሆኑን የሚጠቁም ነው።

የጤናና የአካባቢ ሳይንስ ምሁራን ቆሻሻ ማቃጠል ተገቢ ቢሆንም ተግባሩ ግን በሳይንሳዊ መንገድ መከናወን እንዳለበት ያምናሉ። እንደተፈለገ የትም የሚቃጠል ቆሻሻ አየር ይበክላል። የተበከለ አየር ደግሞ ሰዎችን እንደ አስም ላሉት የመተንፈሻ አካላት በሽታዎች ሊያጋልጣቸው ይችላል። ስለዚህ ቆሻሻን በተለምዶ በማቃጠል ሌላ ቆሻሻ እንዳይፈጠር ዘመናዊ የቆሻሻ አወጋገድ መንገድ መከተል ይገባል።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1."ስፓንሽ ፍሉ" የተከሰተው በየትኛው ክፍለ ዘመን ነው?
2. በተበከለ አየር ምክንያት የሚመጣው በሽታ የትኛው ነው?
3. "ስፓንሽ ፍሉ" መጀመሪያ የተከሰተው የት ነው?

ምንም እንኳን በህዳር ሲታጠን መነሻነት ቆሻሻ ሰብስቦ ማቃጠል የተለመደ ተግባር መሆኑ ቢታወቅም በማቃጠል ሊወገዱ የማይችሉ ቆሻሻዎችን በመቅበር ማስወገድ ይቻላል። ከየቤቱ የሚወጣውንና በየቦታው የሚገኘውን ቆሻሻ ለመቅበር ግን በቅድሚያ የሚበሰብሰውንና የማይበሰብሰውን መለየት ያስፈልጋል። በተለይ እንደፕላስቲኮች፣ ፌስታሎች፣ ስብርባሪ ጠርሙሶች፣ ወዘተ. ያሉት የማይበሰብሱና አፈርን የሚበክሉ ቆሻሻዎች በመሆናቸው ከመቅበር መቆጠብ ያስፈልጋል። ከዚህ ውጭ ያሉትን በቀላሉ ሊበሰብሱ የሚችሉትን ቆሻሻዎች መቅበር ግን ጉዳት አያመጣም። በአጠቃላይ ቆሻሻን ለማጥፋት የህዳር ሲታጠንን የተለምዶ የቆሻሻ

አወጋገድ ዘመናዊ በማድረግ፣ እንዲሁም ቆሻሻን በመቅበር የአካባቢን ፅዳት መጠበቅ ይቻላል።

(ዜና አካባቢ መፅሔት፣ቅፅ 2፣ቁጥር6፣ 2012 ዓ.ም.)

**ክፍለጊዜ ስምንት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልስ ስጡ።

1. የህዳር ሲታጠንን አመጣጥ ታሪክ ግለፁ።
2. ቆሻሻን እንደተፈለገ የትም ቦታ ማቃጠል የማይደገፈው ለምን ይመስላችኋል?
3. በፅሑፉ ውስጥ የተጠቀሱት የቆሻሻ አወጋገድ መንገዶች ምን ምን ናቸው?
4. ቆሻሻን ከመቅበር በፊት አስቀድሞ የሚበሰብሰውንና የማይበሰብሰውን መለየት ለምን ይጠቅማል ትላላችሁ?
5. ጉድጓድ በመቆፈር ቢቀበሩ ጉዳት አያመጡም የተባሉት ቆሻሻዎች የትኞቹ ናቸው?

ለ. የሚከተሉት ሀሳቦች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ “እውነት” ትክክል ካልሆኑ ደግሞ “ሀሰት” በማለት መልሱ።

1. "ህዳር ሲታጠን" ሳይንሳዊ የሆነ ቆሻሻ የማቃጠል ልማድ ነው።
2. ቆሻሻን ማቃጠል ሌላ ቆሻሻ እንዲፈጠር ያደርጋል።
3. ቆሻሻን ማስወገድ የሚቻለው በማቃጠል ብቻ ነው።

4. ቆሻሻን ማቃጠል ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ ነው።
5. ሰዎች ቆሻሻን በማቃጠል የአካባቢያቸውን ፅዳት መጠበቅ የጀመሩት በቅርብ ጊዜ ነው።

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

## መልመጃ ሶስት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን ምረጡ።

1. ቆሻሻን በሳይንሳዊ መንገድ ማስወገድ ይገባል የሚሉት ምሁራን እነማን ናቸው?

   ሀ. የአካባቢ ሳይንስ ሐ. የምግብ ሳይንስ

   ለ. የጤና ሳይንስ መ. ሀ እና ለ መልስ ይሆናሉ

2. ከሚከተሉት በአፈር ውስጥ የማይበሰብሰው ቆሻሻ የቱ ነው?

   ሀ. የጠርሙስ ስብርባሪ ሐ. ቁርጥራጭ ወረቀት

   ለ. የምግብ ትርፍራፊ መ. የተበላሸ አትክልት

3. ከሚከተሉት ውስጥ በመቅበር ማስወገድ የሚቻለው ቆሻሻ የቱ ነው?

   ሀ. ፌስታል ለ. ፕላስቲክ ሐ. ብረት መ. የሙዝ ልጣጭ

## ክፍለጊዜ አስር

**ማስታወሻ**

አቀላጥፎ ማንበብ ቃላትን፣ ሐረጋትንና ዓረፍተነገሮችን በትክክልና በጥሩ አገላለፅ ማንበብ ሲሆን፣ በሐረጋት መካከል ከፊል፣ በዓረፍተ ነገሮች መጨረሻ ሙሉ እረፍት በማድረግ በተገቢው ፍጥነት ሳይሳሳቱ ማንበብን የሚመለከት ነው።

### ተግባር ስድስት

መምህራችሁ በሚመሯችሁ መሰረት ከምንባቡ አንቀጽ ሁለትን በመጠቀም የአቀላጥፎ ማንበብ (በትክክል እና በተገቢው ፍጥነት) ተግባሮችን አከናውኑ።

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

### ተግባር ሰባት

ከዚህ በታች የቀረበውን ጽሁፍ በትክክል፣ በፍጥነትና በተገቢው ድምጸት አንብቡ።

ሰዎች የግል ንፅህናቸውን ለመጠበቅ ልዩ ልዩ እለታዊ ተግባራትን ያከናውናሉ። ሰዎች የቆሸሹ ልብሶቻቸውን ያጥባሉ፤ እጆቻቸውን፣ እግሮቻቸውን፣ ፀጉራቸውንና የሰውነት ክፍሎቻቸውን ያፀዳሉ። ፀጉራቸው ሲያድግ ይስተካከላሉ፤ ይላጫሉ። የእጅና የእግር

ጥፍሮቻቸውን ይቆርጣሉ። በመኖሪያ ቤታቸውም ውስጥ በጋራ የሚገለገሉባቸውን ቁሳቁሶች ያፀዳሉ። የምግብ ማብሰያ፣ ማቅረቢያና መመገቢያ ዕቃዎችን ያጥባሉ። የመፀዳጃ ቤታቸውንም ንፅህና ይጠብቃሉ።

## ትምህርት አራት ፡ መፃፍ

በዚህ ትምህርት ሥር የቀረበውን ተግባርና መልመጃ በመጠቀም አንቀፅ ትፅፋላችሁ፣ የተጓደሉ አረፍተነገሮችን ታሟላላችሁ።

ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

ተግባር ስምንት

ቀደም ሲል በምዕራፍ አንድ ስር ስለአንቀፅ የተማራችሁትን በማስታወስ ሰዎች የግል ንፅህናቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ የሚገልፅ አጭር አንቀጽ ፃፉ። ከዚህ በታች የቀረቡትን መረ ሀሳቦች አንቀጹን በመጻፍ ሂደት ተጠቀሙባቸው።

- የጥርስንጽህና አጠባበቅ
- የጥርስ ሳሙና
- የጥርስ ብሩሽ
- ውሃ
- መፋቂያ

ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

### መልመጃ አራት

**ቀጥሎ በሳጥን ውስጥ ከቀረቡት ቃላት መካከል እየመረጣችሁ ከታች የተጓደሉትን ዓረፍተነገሮች አሟሉ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቆሻሻ | መተላለፍ | በተናጠል | ማስወገድ |
| እንዳይራቡ | መንስኤ | በጋራ | እንዳይዛመት |

1. የግል ንፅህና የሚባለው ሰዎች———— የሚሰሩትን የፅዳት ስራ የሚመለከት ነው።
2. የግልና የአካባቢ ንጽህና በመጠበቅ በሽታ————— ማድረግ ይቻላል።
3. ቆሻሻ ለተላላፊ በሽታዎች ———— መሆን ይችላል።
4. የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ ሰዎች———— የሚሰሩትን የፅዳት ስራ የሚመለከት ነው።
5. በሽታ አምጪ ነፍሳት———— ማድረግ የሚቻለው አካባቢን በማፅዳት ነው።
6. ቆሻሻን በአግባቡ———— አካባቢን ንፁህ ያደርጋል።
7. ዝንቦች ለበሽታ———— አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ ናቸው።

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ክፍል ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ትፈልጋላችሁ፤ በዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላትና ሀረጋት በሌሎች ተክታችሁ ታሳያላችሁ።

**ክፍለጊዜ አስራ አራት**

### መልመጃ አምስት

**ሀ. በ "ሀ" ስር ለተዘረዘሩት ቃላት በ"ለ" ስር ካሉት ተመሳሳይ ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ።**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. መላምት | ሀ. ማዳን |
| 2. ወረርሽኝ | ለ. መበላሸት |
| 3. ዘዴ | ሐ. ወቅታዊ የሆነ |
| 4. መታደግ | መ. የግምት አባባል |
| 5. መበከል | ሠ. ባህል |
| 6. መቆጠብ | ረ. ጠቅላላ |
| 7. ዘመናዊ | ሰ. ተላላፊ በሽታ |
| 8. ልማድ | ሸ. ነባር |
| | ቀ. መተው |
| | በ. ብልሃት |

ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## መልመጃ ስድስት

**ለ. በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት በ"ለ" ስር ካሉት ተቃራኒ ፍቾቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ።**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ቅድሚያ | ሀ. መፍጠር |
| 2. መለየት | ለ. መጠራጠር |
| 3. ማጥፋት | ሐ. መበተን |
| 4. መሰብሰብ | መ. መቀላቀል |
| 5. ማመን | ሠ. መጨረሻ |
| | ረ. መከተል |

**ክፍለጊዜ አስራ ስድስት**

**መልመጃ ሰባት**

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ደምቀው የተጻፉትን ቃላትና ሀረጋት በሳጥን ውስጥ ከተዘረዘሩት በመምረጥ ተክታችሁ አሳዩ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| በዘልማድ | መተግበር | ጥቅም | በዕውቀት |
| በመደባለቅ | ችግር | ንፅህና | ስንፍና |

1. ህዝቡ ቆሻሻን በማቃጠል የአካባቢውን **ፅዳት** መጠበቅ አለበት።
2. ቆሻሻን የማቃጠል ስራ በሳይንሳዊ መንገድ **መከናወን** አለበት።
3. ቆሻሻ ሲቃጠል ጢሱ ከአካባቢው አየር ጋር **በመቀላቀል** አየር ይበክላል።
4. ቆሻሻን **በተለምዶ** ማቃጠል ሌላ ቆሻሻ እንዲፈጠር ያደርጋል።
5. በቀላሉ ሊበሰብሱ የሚችሉ ቆሻሻዎችን መቅበር **ጉዳት** አያመጣም ።

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ሥር በቃላት ውስጥ ያሉትን ቀለሞችና ምዕላዶች ለይታችሁ ታሳያላችሁ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### ማስታወሻ

መነጠል እና ማጣመር

ምሳሌ አንድ ፡ "ቆሻሻ" በሚለው ቃል ውስጥ ያሉት ድምፆች (ቀለም) "ቆ-ሻ-ሻ"የሚሉት ናቸው።

ምሳሌ ሁለት፡ "ተማሪዎች" በሚለው ቃል ውስጥ ያሉት ቅጥያዎች (ምዕላድ) "ተማሪ -ዎች" ናቸው።

- መነጠል ማለት በውስብስብ ቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎችን መለያየት ነው።

ምሳሌ፡ "የማቃጠል" ሲነጣጠል የ-ማቃጠል"ይሆናል።

- ማጣመር ማለት ተነጣጥለው ያሉትን ቅጥያዎች አንድ ላይ ማገናኘት ነው።

**ምሳሌ፡ "ሰው-ኦች-ኡ" ሲጣመር "ሰዎቹ" ይሆናል።**

### መልመጃ ስምንት

**ሀ. የሚከተሉትን ቃላት በድምጽ (በቀለም) ነጣጥላችሁ አሳዩ።**

ምሳሌ፡ ዶሮ ዶ-ሮ

1. ገበሬ
2. ተራራ
3. መኪና
4. ዘዴ
5. ባቄላ

## መልመጃ ዘጠኝ

የሚከተሉትን ቃላት በዋና ቃል እና ቅጥያዎች (ምዕላድ) ነጣጥላችሁ አሳዩ።

ምሳሌ፡ ሀገራችን ሀገር-ኣችን

1. ገበሬዎች
2. ተራራማ
3. መኪናዬ
4. ዘመና

# ምዕራፍ ሶስት፡ ትውፊት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ታሪክን አዳምጣችሁ መልሳችሁ ትናገራላችሁ፤
- በተገቢው ቅላፄ ድምፅን ከፍ አድርጋችሁ ታነባላችሁ፤
- የአንቀፅ አይነቶችን ትለያላችሁ፤
- ለቃላት አገባባዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፤
- ተውሳከ ግሶችን ከዓረፍተነገሮች ውስጥ ትለያላችሁ።

## ትምህርት አንድ ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ሥር ከሚደመጥ ፅሑፍ ማስታወሻ ትይዛላችሁ፤ የቡድን ውይይት ታደርጋላችሁ። ከዚህ አኳያ "የባህል ምንነት" በሚል ርዕስ አንድ ምልልስ ይቀርብላችኋል። እናንተም ከምልልሱ የምታገኙትን ዋና ሃሳብ እየለያችሁ በማስታወሻችሁ ላይ ያዙ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

### የባህል ምንነት

**የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ መልሱ።

1. በአካባቢያችሁ ከምታውቋቸው የባህል ክንውኖች አንዱን በማንሳት ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

2. የአንድን ህብረተሰብ ባህል መንከባከብ ያለበት ማን ይመስላችኋል?

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

አንድ ህብረተሰብ ተለይቶ የሚታወቅበት ባህሉ የሚንፀባረቀው በምን በምን ነው ትላላችሁ?

**ክፍለጊዜ ሁለት**

**የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች**

**መልመጃ አንድ**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ በቃል መልሱ።

1. የባህል ባለቤት ማን ነው?
2. አሁን ያለው ህብረተሰብ ባህሉን ያገኘው ከማን ነው?
3. በምልልሱ ውስጥ ባህል የሚያጠቃልላቸው ነገሮች የተባሉት ምን ምን እንደሆኑ ጥቀሱ።
4. ባህልን ለትውልድ ማስተላለፍ ያስችላል ተብሎ በምልልሱ የተጠቀሰው ዘዴ የትኛው እንደሆነ ጥቀሱ።

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ሥር የመናገር ክሂላችሁን እንድታዳብሩ የሚረዱችሁ ተግባሮች ቀርበውላችኋል። በዚህም መሰረት እንደየትዕዛዛቸው ተግባሮቹን ትሰራላችሁ።

**ክፍለጊዜ ሶስት**

**ተግባር አንድ**

**ሀ. ቀደም ሲል የቀረበላችሁን ምልልስ በማስታወስ ባህል ምን እንደሆነ በቡድን ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ግለፁ።**

**ክፍለጊዜ አራት**

**ተግባር ሁለት**

**ለ. የሚከተለውን ጥያቄ ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ ሥሩ።** መምህራችሁ ምልልሱን ሲያነቡላችሁ በያዛችሁት ማስታወሻ መሰረት አንዳችሁ እንደጠያቂ፣ አንዳችሁ እንደመላሽ ሆናችሁ ምልልሱን እንደገና ተርኩ።

**ክፍለጊዜ አምስት**

**ተግባር ሦስት**

**ሐ. በአካባቢያችሁ ስለሚታወቅ አንድ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ምንነት፣ ከምን እንደሚሰራና ለምን እንደሚጠቅም ጠይቃችሁ የተረዳችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።**

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ሥር ምንባብ ቀርቦላችኋል። ምንባቡን እያነበባችሁ ዋና ዋና ሐሳቦችን ማስታወሻ ትይዛላችሁ። ከዚያም ከምንባቡ ለወጡ የተለያዩ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ትሰጣላችሁ። .

## ክፍለጊዜ ስድስት

## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ሆናችሁ በመወያየት መልሳችሁን በቃል ስጡ።

1. በአካባቢያችሁ ሰዎች ምርቃት ሲመርቁ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ሰምታችሁ ከሆነ ሲመርቁ ምን ምን እንደሚሉ እንደነሱ በመሆን በቃል አሰሙ።
2. በአካባቢያችሁ ምርቃት የሚመርቁት ምን አይነት ሰዎች እንደሆኑ የምታውቁትን አስረዱ።
3. ሰዎች የሚመርቁት በምን ምክንያት ይመስላችኋል?

ቀጥሎ የቀረበውን ፅሑፍ ተገቢነት ባለው ቅላፄ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ አንብቡ።

## ምርቃት

ምርቃት ወደፊት ለሚፈፀም ነገር ይሁንልህ፣ ይደረግልህ ብሎ መመኘት ወይም ተስፋ መስጠት ነው። ተስፋውም በጆሮ የሰሙት እውን እንዲሆን፣ በአይን እንዲታይና በእጅ እንዲዳሰስ ከመመኘት አንፃር ነው። ምርቃት መራቂው በተደሰተ ቁጥር ላስደሰተው ሰው በጎ ነገርን ከመሻት በሚመነጭ የሚሰጠው ቃላዊ ምላሽም ነው። ምንም እንኳን ምርቃት ወደፊት ለሚፈፀም ነገር የሚነገር ምኞት ቢሆንም ተመራቂው ይሆንልኛል ብሎ የሚያምነው ግን በዕለቱ እንደሚፈፀምለት በማመን ነው። በመሆኑም ምርቃት ሰዎች አምነው በተስፋ የሚቀበሉት ልማድ ነው ማለት ነው።

የምርቃት አከዋወን የተለያዩ ገፅታዎች አሉት። ከነዚህም ውስጥ በአብዛኛው የሚታወቀው መራቂውና ተመራቂዎች ፊት ለፊት ቆመው መራቂው የባህሉን ስልት በመጠቀም የሚከናወነው ነው። በዚህ ጊዜ መራቂው ሲመርቅ ተመራቂዎች የእጅ መዳፋቸውን በመዘርጋትና አንገታቸውን ሰበር በማድረግ ጭንቅላታቸውን ወደ ላይና ወደ ታች በማወዛወዝ ምርቃቱን የሚቀበሉበት ነው። ሌላው የምርቃት ገጽታ ደግሞ መራቂው እጁን በተመራቂው ላይ በመጫን የሚያከናውነው ምርቃት ነው። ይህም የሚደረገው ምርቃቱ በሚሰጥበት ጊዜ የመራቂው ምኞት በምስጢራዊ ኃይል በተመራቂው ውስጥ ይሰርፃል ተብሎ ስለሚታመን ነው።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄ

| |
|---|
| እስካሁን ካነበባችኋቸው አንቀጾች በእያንዳንዳቸው ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ሐሳቦች ግለፁ። |

ብዙ ጊዜ በተለያየ አካባቢ ምርቃት ሲመርቁ የሚታዩት ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶችና በተለይ በኦሮሞ የገዳ ሥርዓት ደግሞ "አባ ገዳዎች" ናቸው። ሽማግሌዎች የሚሰጡት ምርቃት ተቀባይነት ይኖረዋል ተብሎ የሚታመንባቸው ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው ምክንያት የሽማግሌዎች ምርቃት በፈጣሪ ፊት ተቀባይነት አለው ተብሎ ስለሚታመን ነው። ሌላው ደግሞ መራቂ ሽማግሌዎች በሚመርቁበት ጊዜ ቋንቋውን ስለሚያስውቡት

ተመራቂዎችም “ይሰማልናል” ወይም “ይፈፀምልናል” የሚል እምነት ስለሚያድርባቸው ነው።

ምንጭ፡ (ትንሣኤ ጀምበሬ፣ ዲማፅ 2002 ዓ.ም. በመጠኑ ተሻሽሎና ለክፍል ደረጃው እንዲመጥን ተደርጎ የተወሰደ።)

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ።**

1. ምርቃት ምን እንደሆነ አብራሩ።
2. ተመራቂው ምርቃት ሲወስድ መቼ ይፈፀምልኛል ብሎ ያስባል?
3. በአብዛኛው የሚታወቀው የምርቃት አከዋወን ገጽታ የትኛው ነው?

**ክፍለጊዜ ስምንት**

### መልመጃ ሶስት

**ለ. የሚከተሉት ሀሳቦች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ።**

1. ትውፊት በውስጡ የሚያካትታቸው ዝርዝር ጉዳዮች ጥቂት ናቸው።
2. ምርቃት የሚሰጠው ለሰዎች በጎ ነገርን ከመሻት ነው።

3. የሸማግሌዎች ምርቃት በፈጣሪ ፊት ተቀባይነት አለው ተብሎ ይታመናል ።
4. ብዙ ጊዜ ምርቃት ሲመርቁ የሚታዩት ሽማግሌዎች ብቻ ናቸው።

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

## መልመጃ አራት

**ሐ. በ "ሀ"ምድብ ለተዘረዘሩት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ "ለ" ምድብ በመምረጥ አዛምዱ።**

| " ሀ " | " ለ " |
| --- | --- |
| 1. መመኘት | ሀ. ምኞት |
| 2. እውን | ለ. ገሃድ |
| 3. ተስፋ | ሐ. ገባ |
| 4. ምስጢር | መ. መፈለግ |
| 5. ሰረፀ | ሠ. ማሳመር |
| 6. ማስዋብ | ረ. እውነት |
| | ሰ. ድብቅ |

**ክፍለጊዜ አስር**

## መልመጃ አምስት

**መ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ተስማሚውን መልስ ምረጡ።**

1. በአብዛኛው በሚታወቀው የምርቃት አሰጣጥ ላይ የማይከናወነው ተግባር የትኛው ነው?

ሀ. አንገት መስበር　　　　ሐ. ጭንቅላት ማወዛወዝ

ለ. እጅ መጫን　　　　　መ. የእጅ መዳፍ መዘርጋት

2. ከሚከተሉት ውስጥ ምርቃት የማይመርቁት እነማን ናቸው?

ሀ. ሽማግሌዎች　　　　ሐ. የሀይማኖት አባቶች

ለ. አባ ገዳዎች　　　　መ. የመንግስት ባለስልጣኖች

3. ምርቃት መልስ ያገኛል ተብሎ የሚታመነው ማን ጋ ነው?

ሀ. መራቂ　　　　　　ሐ. ሽማግሌዎች

ለ. ተመራቂ　　　　　መ. መልሱ አልተሰጠም

## ትምህርት አራት፡ መፃፍ

በዚህ ትምህርት ሥር የመጻፍ ክሂላችሁን እንድታዳብሩ የተለያዩ ተግባሮች ስለቀረቡላችሁ በተሰጣችሁ ትዕዛዞች መሰረት ትሰራላችሁ።

**ክፍለጊዜ አስራ አንድ**

**የአንቀፅ አይነቶች**

1. **ተራኪ አንቀፅ፡** የአንድን ነገር ክንውን በጊዜ ቅደም ተከተል እንዲህ ሆነ፤ እንዲህ ተደረገ እያለ ይተርካል።

**ምሳሌ ፡** የህይወት ታሪክ የሚፃፈው በተራኪ አንቀጽ ስልት ነው።

2. **ስዕላዊ አንቀፅ፡** አንባቢው የሚያነበውን ነገር ምስል በአእምሮው እንዲስል የሚያስችል ነው።**ምሳሌ፡** የቢሮ ፀሐፊዋ ሽቶዋ ያውዳል።

ጥቁር ሹራብ ለብሳለች።...

3. **አመዛዛኝ /አከራካሪ አንቀፅ፡-** ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተቃራኒ ሀሳቦችን በማመዛዘን የትኛው እንደሚሻል የሚያሳይ ነው።

**ምሳሌ፡** የዱሮ ሴቶች ምግባቸውን የሚያበስሉት በማገዶ ነው። የአሁን ሴቶች ግን ምግባቸውን የሚያበስሉት በጋዝ ወይም በኤሌክትሪክ ምድጃ ነው።

**ክፍለጊዜ አስራ ሁለት**

**ተግባር አራት**

ከላይ ከቀረቡት የአንቀፅ አይነቶች አንዱን ስልት መርጣችሁ በፈለጋችሁት ርዕስ አንድ አንቀፅ ፃፉ።

**ክፍለጊዜ አስራ ሶስት**

**ተግባር አምስት**

በአካባቢያችሁ ስለምታውቁት ጥሩ ወይም መጥፎ ልማዳዊ ድርጊት ከተማራችኋቸው የአንቀፅ አይነቶች አንዱን በመምረጥ አንቀፅ ፃፉ።

## ትምህርት አምስት፡ቃላት

በዚህ ትምህርት ሥር ለተለያዩ ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንድትሰጡ፣ በአዳዲስ ቃላት ዓረፍተነገር እንድትመሰርቱ፡ እንዲሁም፣ ለቃላት

መዝገበቃላዊ ፍች እንድትፈልጉ የሚያስችሏችሁ መልመጃና ተግባሮች ስለቀረቡ በትኩረት ስሩ።

ክፍለጊዜ አስራ አራት

## መልመጃ ስድስት

**በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ደምቀው ለተጻፉት ቃላት አገባባዊ ፍች ስጡ።**

1. ያለእድሜ ጋብቻ በአእምሮ **ሳይበስሉ** የሚፈፀም ነው።
2. የሽምግልና አላማ ችግርን **መፍታት** ነው።
3. የዕድር መተዳደሪያ ደንብ በአባላት **ፀደቀ**።
4. የዕድር አባላት **በቋሚነት** ሊታገዙ ይገባል።

ክፍለጊዜ አስራ አምስት

**ተግባር ስድስት**

መምህራችሁ ሁለት ምልልሶችን ያነቡላችኋል። እናንተም በምልልሶቹ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት ለይታችሁ መዝግቡ። ከዚያም ቃላቱን ዓረፍተነገሮች ውስጥ በማስገባት አገባባዊ ፍቻቸውን ግለፁ።

ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

**ተግባር ሰባት**

ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ቃላት መዝገበቃላዊ ፍች ፈልጉላቸው፡፡

1. መረቀ
2. አወደ
3. ሸመገለ
4. ዕድር
5. ጠቃሚ

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ሥር ተውሳከግሳዊ ተግባር ያላቸውን ቃላትና ሀረጋትን ትለያላችሁ።

ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

**ማስታወሻ**

ተውሳከግስ ግስን ለመግለጽ የሚገባ ቃል ወይም ሀረግ ነው።

ግስን የሚገልጸውም ከጊዜ፣ ከቦታ፣ ከሁኔታ፣ ወዘተ. አንጻር ነው።

ምሳሌ፡ ፍራኦል ትናንት መጣ ። (ጊዜን ይገልጻል)

ቦንቱ እዚህ ነበረች። (ቦታን ይገልጻል)

ዘይነባ በፍጥነት መጣች። (ሁኔታን ይገልጻል)

ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

### መልመጃ ሰባት

**ቀጥሎ ባሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ተውሳከግሶች ከስራቸው በማስመር ለይታችሁ አመልክቱ።**

1. ገመቹ ዛሬ መጣ ።
2. ፍሮምሳ ወደ አዳማ ሄደ።
3. ነኢማ ከነቀምቴ መጣች።
4. ከድር ሁልጊዜ ያጠናል።
5. ጋዲሴ ቶሎ ሄደች።
6. ፈተናው ገና ይሠጣል፡፡
7. እሱ ክፉኛ ወደቀ።
8. ልጅቱ ምንኛ ታምራለች።

# ምዕራፍ አራት፡ የመንገድ ደህንነት


### የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ፡-**

- ምልልስን አዳምጣችሁ የምልልሱን ጠቀሜታ መልሳችሁ ትናገራላችሁ፤
- ፍች ላይ ለመድረስ የተለያዩ የአዳምጦ መረዳት ብልሃቶችን ትጠቀማላችሁ፤
- ማህበራዊ አገላለፆችን ትጠቀማላችሁ፤
- የቀረበውን አንቀፅ ጭብጥ፣ ፍች እና አላማ ታስረዳላችሁ።

## ትምህርት አንድ ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ሥር የመንገድ ትራፊክ አደጋ እና የመከላከያ ጥንቃቄዎችን በተመለከተ ምልልስ ቀርቦላችኋል። ምልልሱን አዳምጣችሁ መልመጃዎችን ትሰራላችሁ፤ የምልልሱን ዋና ሃሳብ እየለያችሁ ማስታወሻችሁ ላይ ትመዘግባላችሁ።



**ክፍለጊዜ አንድ**

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. የመንገድ ትራፊክ አደጋ ማለት ምን ማለት ነው? በቡድን ተወያይታችሁ መልሱ።
2. በአካባቢያችሁ የመንገድ ትራፊክ አደጋ ደርሶ ያውቃል? መልሳችሁ አዎን ከሆነ የደረሰው አደጋ ምንድን ነው?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የመንገድ ትራፊክ አደጋ ሊከሰት የሚችለው በ——— እና በ———ነው።
2. የመንገድ ትራፊክ አደጋ ጉዳቱ የሚያርፈው በ———፣ በ——— እና በ——— ላይ ነው።
3. የምልልሱን ዋና ዋና ሃሳቦች ማስታወሻ እየያዛችሁ አዳምጡ።

## የአዳምጠ መረዳት ጥያቄዎች

**ክፍለጊዜ ሁለት**

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት ምልልስ መሰረት በቡድን ተወያይታችሁ ምላሹን በቃል ስጡ።

1. እግረኞች ከመንገድ ትራፊክ አደጋ ራሳቸውን መጠበቅ ያለባቸው እንዴት ነው?
2. እግረኞች የእግረኞች መንገድ ባልተዘጋጀበት አካባቢ መጓዝ ያለባቸው እንዴት ነው?

3. ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀስ የማይፈቀድላቸው በየትኛው መንገድ ላይ ነው?
4. ዜብራ ምንድን ነው?

**ክፍለጊዜ ሶስት**

**ተግባር አንድ**

1. በትራፊክ አደጋ መንስኤዎች እና መፍትሔዎቻቸው ላይ ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።
2. የትራፊክ አደጋ ሲደርስ በአካባቢው ብትኖሩ ምን እንደምታደርጉ በቡድናችሁ ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ሃሳብ በቃል ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

**ክፍለጊዜ አራት**

## ትምህርት ሁለት ፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ሥር የተለያዩ ስዕሎች ይቀርቡላችኋል። ስዕሎቹን መሰረት በማድረግ የቀረቡትን ተግባሮች በትእዛዞቹ መሰረት ትሰራላችሁ።

**ተግባር ሁለት**

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች እንደአጠያየቃቸው ተገቢውን መልስ በቡድን እየተወያያችሁ ስጡ።**

ሀ. በማዳመጥ ሂደት ከቀረበላችሁ ምልልስ ያገኛችሁትን ዋና ሀሳብ መልሳችሁ ተናገሩ።

ለ. ከዚህ በታች የትራፊክ አደጋን የሚያሳዩ የተለያዩ ስዕሎች ቀርበዋል። እናንተም እያንዳንዱን ስዕል በመመልከት ስለአደጋው የተረዳችሁትን በቅደም ተከተል ለመምህራችሁ ተናገሩ።



1



2



3



4

## ክፍለጊዜ አምስት

### ተግባር ሶስት

ሐ. የትራፊክ ህጎችን በተመለከተ በጥንድ በመሆን ምልልስ አዘጋጅታችሁ ለክፍሉ ተማሪዎች ምልልሱን አቅርቡ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

### ተግባር አራት

መ. ከዚህ በታች ሁለት አይነት የትራፊክ መብራቶችን የሚያሳዩ ምስሎች ቀርበዋል። እናንተም የትራፊክ መብራቶቹን በተመለከተ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ።

ምስል 1፡ የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ የትራፊክ መብራቶች




## ክፍለጊዜ ሰባት

ምስል 2፡ የእግረኛ ማስተላለፊያ የትራፊክ መብራቶች



1. ቀይ መብራት ሲበራ ምን የሚል ትዕዛዝ ያስተላልፋል?
2. አረንጓዴ መብራት ሲበራ ምን ያስተላልፋል?

ክፍለጊዜ ስምንት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ክፍል የመንገድ ትራፊክ ደህንነት በሚል ርዕስ ምንባብ የቀረበላችሁ ሲሆን ከስሩም የተለያዩ መልመጃዎችና ተግባሮች ተሰጥተዋል። በመሆኑም በትዕዛዛቸው መሰረት በትኩረት ስሩ።

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥንድ በመወያየት በቃል መልሱ።**

1. ስለትራፊክ ምን ታውቃላችሁ?
2. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማለት ምን ማለት ነው?

**ማስታወሻ**

**የለሆሳስ ንባብ**

ድምፅ ሳታሰሙ (በለሆሳስ) በግላችሁ ፅሑፍ ስታነቡ፣ ከንፈር ሳታንቀሳቅሱ፣ ፅሁፉን በጣታችሁ ሳትጠቁሙ ማንበብ አለባችሁ። ምክንያቱም እነዚህ ልምዶች የንባብ ፍጥነታችሁንና የመረዳት ችሎታችሁን ስለሚቀንሱ ነው።

የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማለት ትራፊክና የመንገድ ትራፊክ ደህንነት የሚሉትን የያዘ ነው። ትራፊክ የሚለው ቃል ተንቀሳቃሽ ወይም ተላላፊ ማለት ነው። ይህም በአየር፣ በባህርና በየብስ ተለይተው በሚታወቁ መስመሮች ላይ የሚንቀሳቀሱትን

ይመለከታል። የአውሮፕላን፣ የመርከብ፣ የባቡር፣ የተሽከርካሪ፣ የሰውና የእንስሳት እንቅስቃሴ ዝውውርን ትራፊክ እንላለን። ትራፊክ የአየር ትራፊክ፣ የባህር ትራፊክና የየብስ ትራፊክ በማለት በሶስት ይከፈላል። ለምሳሌ የየብስ ትራፊክ ባለሞተርና የሞተር አልባ ተሽከርካሪዎችን እና የባቡር እንቅስቃሴ ዝውውርን የሚመለከት ነው። የመንገድ ትራፊክ ደህንነት የሚለው ደግሞ የመንገድ **ተጠቃሚዎች** ከማንኛውም የመንገድ ላይ ችግር ነፃ መሆንን የሚያሳይ ነው። የመንገድ ተጠቃሚዎች ተብለው የሚታወቁት እግረኞች፣ አሽከርካሪዎችና ተሳፋሪዎች ናቸው። የመንገድ ላይ ችግሮች ደግሞ ሞት፣ የአካል ጉዳትና የንብረት **ውድመት** ናቸው።

ለመንገድ ትራፊክ አደጋ መድረስ የተለያዩ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። ከነዚህም ውስጥ በሰዎች ስህተትና **ቸልተኝነት** የሚደርሰው አደጋ አብላጫውን ይይዛል። በተሽከርካሪ ክፍሎች ላይ በሚደርስ **ብልሽት** የሚከሰተውም አደጋ ቀላል አይደለም። በመንገዶች የተፈጥሮ አቀማመጥ ማለትም **ጠመዝማዛ** መሆን የሚከሰት አደጋም አለ። የአየር ንብረት ችግርና የመንገድ ላይ ህገወጥ ንግድም እንደደረጃቸው ተጠቃሾች ናቸው። ይሁን እንጂ በአሽከርካሪ እና በእግረኛ ስህተት የሚፈጠረው አደጋ ከሁሉም ይበልጣል። በመሆኑም በአሽርካሪና በእግረኛ ስህተት የሚከሰተውን አደጋ በዝርዝር **መቃኘት** ለጥንቃቄ ይረዳል።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

ቀጥሎ የቀረበውን ፅሑፍ ድምፅ ሳታሰሙ (በለሆሳስ) በግላችሁ አንብቡ። ከዚያም የፅሑፉን ዋና ዋና ሀሳቦች በማስታወሻ ደብተራችሁ አስፍሩ።

የ———፣ የ———፣ የ———፣ የ——— እና የ———እንቅስቃሴ ዝውውርን ትራፊክ ይባላል።

1. ትራፊክ የ———፣ የ——— እና የ——— በመባል በሶስት ይከፈላል።

የአሽከርካሪ ስህተት የምንለው አሽከርካሪዎች በሚያሽከረክሩበት ወቅት ህግና ደንብን በመተላለፍ የሚፈፅሙት ነው። ይህም ማለት አሽከርካሪዎች ህጎችና ደንቦች ባለማክበራቸው ምክንያት የሚመጣ አደጋ ነው። በዚህ አደጋም የራሳቸውንና የወገናቸውን ህይወት እስከመቅጠፍ ያደርሳቸዋል። አሽከርካሪዎች ከሚፈፅሟቸው ስህተቶች መካከል የሚጠቀሰው ከፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር ነው። ሌላው ደግሞ እግረኛው መንገድ በሚያቋርጥበት ጊዜ ለእግረኛው ቅድሚያ አለመስጠት ነው። አልኮል ጠጥቶ ሰክሮ ማሽከርከርና አደንዛዥ ዕፅ መጠቀምም እንደ ስህተተ የሚቆጠር ነው። እንዲሁም እንቅልፍ ሳይተኙ በድካም ስሜት ማሽከርከር ለአደጋ የሚያጋልጥ ነው።

የእግረኛ ስህተት የምንለው ደግሞ እግረኞች መንገድ ላይ በሚሄዱበት ጊዜ የሚፈፅሟቸው ናቸው። እነዚህ ስህተቶች

**እግረኞችን ለአደጋ ተጋላጭ ሲያደርጋቸው ክቡሩን ህይወታቸውን እስከማጣት ያደርሳቸዋል። እግረኞች ከሚፈፅሟቸው ስህተቶች ውስጥ አንዱ ተሽከርካሪ መቆሙን ሳያረጋግጡ መንገድ ለመሻገር መሞከር ነው። በሌላ በኩል ተሽከርካሪ ተከልሎ መንገድ ማቋረጥና ጀርባ ሰጥቶ መሄድም ይጠቀሳል። በተጨማሪም ለእግረኛ ባልተፈቀደ መንገድ መሻገርና በእግረኛ መንገድ አለመጠቀም ሌላው ስህተት ነው። በተለይ የትራፊክ መብራትንና ምልክቶችን አለማክበር ደግሞ እንደ ዐብይ ስህተት ይታያል ።**

(በትምህርት ቤቶች የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማኑዋል ከሚለው ተሻሽሎ የተወሰደ)

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. ከዚህ ቀጥሎ ምንባቡን መሰረት አድርገው ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ።

1. እግረኞች በመኪና መንገድ ላይ ለተሽከርካሪ ጀርባ ሰጥተው መሄድ የሌለባቸው ለምንድን ነው?
2. አሽከርካሪዎች ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት ያለባቸው መቼ ነው?
3. በፅሑፉ ውስጥ የመንገድ ላይ ችግሮች ተብለው የተጠቀሱት በስንተኛው አንቀፅ ላይ ነው?

4. በምንባቡ ውስጥ ‹‹የወገናቸውን ህይወት **እስከመቅጠፍ** …›› የሚለው ሐረግ ምን ይገልጻል?
5. ለመንገድ ትራፊክ አደጋ መከሰት አጋላጭ ምክንያቶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?
6. በምንባቡ ሀሳብ መሰረት ርዕሱ ምን ይሆናል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ለ. የሚከተሉት ሀሳቦች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. የመንገድ የተፈጥሮ አቀማመጥ ለመንገድ ትራፊክ አደጋ መከሰት አንዱ ምክንያት ነው።
2. በቂ እንቅልፍ አለመተኛት ለመንገድ ትራፊክ አደጋ ያጋልጣል።
3. እግረኞች መንገድ ማቋረጥ ያለባቸው የእግረኛ መንገድ በመጠቀም ነው።
4. እግረኞች በመንገድ ላይ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ክቡሩን ህይወታቸውን እስከማሳጣት ያደርሳቸዋል።
5. አልኮል ጠጥቶ ማሽከርከር አሽከርካሪዎችን የሚጠቅም ተግባር ነው።

## ትምህርት አራት፡ መፃፍ

በዚህ ትምህርት ሥር ስለመንገድ ደህንነት ገላጭ አንቀፅ የሚያፅፏችሁ ተግባሮች ቀርበዋል። በመሆኑም ትዕዛዞቹን በመከተል ጻፉ።

## ክፍለጊዜ አስር

### ተግባር አምስት

ቀደም ሲል ከቀረበው ትምህርት ስለመንገድ ደህንነት የተረዳችሁትን ነገር ከ30 ባላነሱ ቃላት ገላጭ አንቀጽ ፃፉ።

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

### ተግባር ስድስት

**ማስታወሻ**

**ገላጭ አንቀፅ**

ገላጭ አንቀፅ ስለማንኛውም ነገር ምንነት፣ ባህሪይ፣ የአሰራር ቅደም ተከተል ለማብራራት የሚፃፍ ነው። ይህም ማለት ስለሚገለፀው ጉዳይ በዝርዝር ማስረዳት ወይም መተንተን ነው።

ከዚህ በታች ገላጭ አንቀጽ ቀርቦላችኋል። አንቀጹን መሰረት በማድረግ አስቀድማችሁ አያያዦችን ለዩ። በመቀጠል አገልግሎታቸውን ግለጹ። በመጨረሻም በድርጊት ቅደም ተከተል የአንቀጹን ሀሳብ አሳጥራችሁ ጻፉ።

መንገድ ስናቋርጥ መፈጸም የሚገቡን ተግባሮች አሉ። በቅድሚያ መንገድ ከማቋረጣችን በፊት የእግረኛ ማቋረጫ ‹‹ዜብራ›› መኖሩን ማረጋገጥ አለብን። እንዲሁም ተላላፊ ተሽከርካሪዎች በቅርብ መኖር አለመኖራቸውን በስተግራ እና በስተቀኝ ማየት

ያስፈልጋል። በመቀጠል ዜብራውን በፍጥነት እየተራመድን ማቋረጥ ተገቢ ይሆናል። በመጨረሻም የግራ መስመራችንን ይዘን ወደ ምንፈልግበት ስፍራ ለእግረኛ በተዘጋጀው መንገድ መጓዝ ይኖርብናል።

**ክፍለጊዜ አስራ ሁለት**

**ተግባር ሰባት**

ከላይ በቀረበው ናሙና ፅሑፍ መሰረት ‹‹የእግረኛ ማስተላለፊያ የትራፊክ መብራት አጠቃቀም›› በሚል ርዕስ በስምንት አረፍተነገሮች የተዋቀረ አንድ ገላጭ አንቀፅ ፃፉ።

**ክፍለጊዜ አስራ ሶስት**

## ትምህርት አምስት ፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ክፍል የቃላት መዝገበቃላዊ ፍች የሚያለማምዳችሁ ተግባር ቀርቧል። ስለዚህ በተሰጣችሁ ትዕዛዞች መሰረት ስሩ።

**ተግባር ስምንት**

ሀ. ለሚከተሉት ቃላት በአቅራቢያችሁ ወደሚገኝ ቤተመጻሕፍት በመሄድ የአማርኛ መዝገበቃላት ተጠቅማችሁ ተመሳሳይ ፍቻቸውን ፈልጉ።

1. ንብረት
2. አደጋ
3. አሽከርካሪ
4. ህይወት
5. እግረኛ
6. ወገን
7. ማቋረጫ
8. መከለል

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

### መልመጃ ሶስት

ሀ. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ቀጥተኛ ፍች ከሰጣችሁ በኋላ ከላይ ባነበባችሁት ምንባብ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ፍች ስጡ።

| | | |
|---|---|---|
| 1. የብስ | 5. ብልሽት | 9. ተጋላጭ |
| 2. ውድመት | 6. ጠመዝማዛ | 10. ዐብይ |
| 3. ቸልተኝነት | 7. መቃኘት | 11. ህገወጥ |
| 4. ተጠቃሚዎች | 8. ወሰን | 12. ከለከለ |

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

ለ. በሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ደምቀው የተጻፉትን ቃላት ፍቻቸውን በሚያሳዩ ሌሎች ቃላት ተክታችሁ አሳዩ።

1. በሰዎች ስህተትና ቸልተኝነት የሚደርሰው አደጋ **አብላጫውን** ቁጥር ይይዛል ።
2. ለመንገድ ትራፊክ አደጋ መድረስ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ።
3. አሽከርካሪዎች ህጎችና ደንቦች ባለማክበራቸው ምክንያት የወገናቸውን ህይወት እስከ **መቅጠፍ** ያደርሳቸዋል።
4. አልኮል ጠጥቶ ሰክሮ ማሽከርከርና አደንዛዥ ዕፅ መጠቀም እንደ ስህተት **የሚቆጠር** ነው።
5. የአሽከርካሪ ስህተት የምንለው አሽከርካሪዎች በሚያሽከረክሩበት ወቅት ህግና ደንብን **በመተላለፍ** የሚፈፅሙት ነው።
6. እግረኞች የሚፈፅሟቸው **ስህተቶች** የተለያዩ ናቸው፡

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ሥር የሁኔታ አመልካች ተውሳከግሶችን በዓረፍተ ነገር ውስጥ እንድትጠቀሙ የሚረዳችሁ ማስታወሻ እና ተግባሮች ቀርበውላችኋል። ስለሆነ በተሰጡት ትእዛዞች መሰረት ስሩ።

**ክፍለጊዜ አስራ ስድስት**

**ማስታወሻ**

**የሁኔታ ተውሳከግስ**

የሁኔታ ተውሳከግስ በግሱ የተገለፀው ድርጊት እንዴት እንደተፈፀመ የሚያመለክት ነው።

ምሳሌ፡ ፋጡማ **በዝግታ** ተራመደች ።

"**በዝግታ**" የሚለው የፋጡማን የአረማመድ ሁኔታ የሚገልፅ ነው።

## መልመጃ አራት

ሀ. የሚከተሉትን ሁኔታ አመልካች ተውሳከግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገሮች መስርቱ።

ምሳሌ፡

ክፉኛ፡ ዛሬ በደረሰው የመኪና አደጋ ብዙ ሰዎች **ክፉኛ** ተጎድተዋል።

1. በፍጥነት
2. በድንገት
3. በጀግንነት
4. በትጋት
5. ምንኛ
6. እየሮጠች
7. በቀስታ

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ አምስት

ለ. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን የሁኔታ ተውሳከ ግሶች ከስራቸው በማስመር ለዩ።

ምሳሌ፡ ዝናብ ስላልጣለ ወንዙን <u>በቀላሉ</u> ተሻገርኩ።

1. አትሌቷ የሩጫ ውድድሩን በብልሀት አሸነፈች።
2. ቶለሳና ቶለሺ የጋራ ንብረታቸውን በስምምነት ተከፋፈሉ።
3. እናት ልጆቿን በእንክብካቤ ታሳድጋለች።
4. ሀሊማ ትምህርቷን በትኩረት ትከታተላለች።
5. ጤነኛ ሰው ስራውን በቅልጥፍና ይሰራል።
6. አስተዋይ ሹፌር መኪናውን የሚያሽከረክረው በጥንቃቄ ነው።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

### መልመጃ ስድስት

ሐ. ቀጥሎ በ "ሀ "ምድብ የቀረቡትን ጅምር የዓረፍተነገር ክፍሎች ሊያሟሉ የሚችሉትን ከ "ለ" ምድብ መርጣችሁ አዛምዱ።

ምሳሌ፡ አብራሪዋ የአውሮፕላኑን ሞተር በድንገት ስለጠፋባት…

መልስ፡ የመከስከስ አደጋ ደረሰባት።

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. እግረኛዋ አደጋ ስለደረሰባት | ሀ. አደጋ አጋጥሟት አያውቅም |
| 2. ፖሊሱ ታታሪ ስለሆነ | ለ. ወደ ሆስፒታል ተወሰደች |
| 3. ተማሪው መንገድ ሲያቋርጥ | ሐ. ብዙ መኪናዎች ቆመዋል |
| 4. ሹፌሯ ጥንቃቄ ስለምታደርግ | መ."ዜብራ"ይጠቀማል |

5. መንገዱ ስለተበላሸ
6. ሹፌሩ በፍጥነት ስለነዳ
7. የትራፊክ ህግ ስለጣሰች

ሠ. ማዕረግ ተሰጠው
ረ. በገንዘብ ተቀጣች
ሰ. የመገልበጥ አደጋ ደረሰበት

**ተግባር ዘጠኝ**

መ. የሚከተሉትን ጅምር የዓረፍተነገር ክፍሎች ተገቢ በሆኑ ሀረጋት አሟሉ።

ምሳሌ፡ የጓደኛዋን መሞት ስትሰማ…

መልስ፡ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች።

1. ተማሪዋ ስላጠናች…
2. የአንበሳውን ድምፅ ስትሰማ…
3. ታታሪዋ መምህራችን ስለተጠራች…
4. ገበሬው ጠንክሮ ስለሰራ…
5. ፋጡማ ስትመጣ…
6. መሐመድ ስለመጣልኝ…

# ምዕራፍ አምስት፡ አካባቢ ጥበቃ

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ፅሑፍ ከቀደመ እውቀታችሁና ልምዶቻችሁ ጋር ታዛምዳላችሁ፤
- መዝገበቃላትን ወይም የቃላት ዝርዝርን በመጠቀም የሆሂያት አሰዳደርን፣ ፍችንና የቃላት እርባታን ትለያላችሁ፤
- በክፍል ደረጃው የመፃፍ ተግባር ወቅት ድምፀት አመልካቾችን ትጠቀማላችሁ።

## ትምህርት አንድ፡ማዳመጥ

ቀጥሎ ስለተፈጥሮ እና የአካባቢ ሚዛን መጠበቅ በሚል ጉዳይ የተዘጋጁ የማዳመጥ ግብዓት እና መልመጃዎች ቀርበውላችኋል። በመሆኑም የቀረቡትን መልመጃዎች ትዕዛዞቹን በመከተል በትኩረት ስሩ።

### የተፈጥሮና የአካባቢ ሚዛን መጠበቅ

**ክፍለጊዜ አንድ**

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ድርቅ የሚከሰተው በምን ምክንያት ይመስላችኋል?
2. ሰዎች አካባቢያቸውን ለመንከባከብ ምን ሲያደርጉ አይታችሁ ታውቃላችሁ?

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የእርሻ መሬትን ለማስፋፋት፣ ———፣ ———፣ ——— ወዘተ. ሲባል በደን ላይ ጭፍጨፋ ሲካሄድ ኖሯል።
2. የመሬት መራቆት——— እና ——— ን ያጠፋል።
3. በአካባቢ ጥበቃ ግንባር ቀደም ተሳታፊ ——— ክፍል ነው።

# የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

ክፍለጊዜ ሁለት

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት መሠረት በቃል መልሱ።

1. ለድርቅ መባባስ ምክንያት የሚሆነው ምንድን ነው?
2. ከግንዛቤ ማነስ የተነሳ በአካባቢና በተፈጥሮ መካከል ያለው ግንኙነት ተጠብቆ አለመራመዱ ምን ውጤት ያስከትላል?
3. የደን መጨፍጨፍ የሚያስከትለው ችግር ምንድን ነው?
4. የአፈር መሸርሸር የሚያመጣውን ጉዳት ለመከላከል ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?
5. ‹‹የመሬት መራቆት›› የሚለው ሀረግ ፍች ምንድን ነው?

### ተግባር አንድ

1. የደን መጨፍጨፍ የሚያስከትላቸው ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሃሳብ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ተማሪዎች በቃል አቅርቡ።

2. በሰው ልጅ እና በአካባቢ መካከል የተፈጥሮ ሚዛን አለመጠበቁ ምክንያቶቹና ጉዳቶቹ ላይ ከሕብረተሰብ ሳይንስ መምህራችሁ መረጃ በመጠየቅ ካደራጃችሁ በኋላ ሀሳቡን ለክፍል ተማሪዎች በቃል አጋሩ።

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ክፍል ሥር መናገርን የሚያበረታቱ ተግባሮች ስለቀረቡላችሁ በትዕዛዞቹ መሰረት ስሩ።

**ክፍለጊዜ ሶስት**

**ተግባር ሁለት**

ሀ. በመምህራችሁ የተነበበላችሁን ጽሁፍ እንደገና በማስታወስ በቃል ተርኩ።

**ክፍለጊዜ አራት**

**ተግባር ሦስት**

ለ. ስለ "አረንጓዴ አሻራ" መርሃ ግብር ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች መረጃ ካሰባሰባችሁ በኋላ በቡድን በማደራጀት በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

**ክፍለጊዜ አምስት**

# ትምህርት ሶስት፡ማንበብ

በዚህ ትምህርት ሥር አካባቢ ጥበቃ በሚል ርዕስ ምንባብ እንዲሁም መልመጃዎች እና ተግባሮች ቀርበውላችኋል። ስለዚህ በቀረቡት ትዕዛዞች መሰረት ስሩ።



## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸውና በቃል መልሱ።

1. አካባቢን መንከባከብ ምን ጥቅም አለው ትላላችሁ?
2. የምታውቋቸው የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች ምን ምን እንደሆኑ ግለፁ።
3. አካባቢን ባለመጠበቅ ሊመጡ የሚችሉ አደጋዎች ምን ምን ናቸው?

በማንበብ ሂደት "አካባቢ ጥበቃ" የሚለውን ምንባብ ድምፃችሁን ከፍ በማድረግ ተራ በተራ አንብቡ። በምታነቡበት ጊዜ ደምቀው የተጻፉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ድምፆች በመነጠልና በማጣመር ለማንበብ ሞክሩ።

## አካባቢ ጥበቃ

አቶ ሁንዴና ወይዘሮ ሶሬቲ በአካባቢያቸው የሚገኘውን የተፈጥሮ ሀብት መንከባከብ ይወዳሉ። አቶ ሁንዴ አንድ ዛፍ ሲቆርጡ ሁለት ችግኞችን **በመትከል** መልሰው ይተካሉ። **ባለቤታቸውም** ቢሆኑ የማገዶ እንጨት ሲለቅሙ **የደረቀውን** እንጨት ካልሆነ በስተቀር እርጥቡን እንጨት አይነኩም። በመሆኑም አካባቢያቸው ሁልጊዜ ልምላሜ የተላበሰ ነው። አረንጓዴ ገጽታ ስላለውም ለአይን ይማርካል።

በሌላም በኩል አቶ ሁንዴና ባለቤታቸው ሃይለኛ ዝናብ ሲዘንብ **በሚያስከትለው** ጎርፍ አፈር ታጥቦ እንዳይሄድ በማሰብ አስቀድመው የተለያዩ የመከላከል ***ሥራዎችን*** ይሠራሉ። ከነዚህም ውስጥ አንዱ ***ዳገታማ*** የሆኑ ቦታዎችን በመቆፈር እርከን ያበጃሉ። እንዲሁም የአካባቢውን ህብረተሰብ በማሳተፍ በክረምት ወራት ችግኞችን ይተክላሉ። የተተከሉ ችግኞችም **እንዲፀድቁ** ለማድረግ **ከከብቶች** ንክኪ ይጠብቋቸዋል። በዚህም የተነሳ የአካባቢው ህብረተሰብ ለም በሆነና ተስማሚ የአየር ጠባይ ባለበት ሥፍራ እንዲኖር አድርገዋል። በተጨማሪም ህብረተሰቡ ንፁህ አየርና በቂ

ዝናብ እንዲያገኝ ምክንያት ሆነዋል። ኑሮውንም በተደላደለና ደስታ በተሞላበት ሁኔታ እንዲመራ አስችለዋል።

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. ካነበባችሁት አንቀጾች ውስጥ ደምቀው የተጻፉ ቃላትን ለይታችሁ በማውጣት በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ መዝግቡ።
2. እስከአሁን ካነበባችሁት ደምቀው የተጻፉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር እንደገና አንብቡ።

በተለይ አቶ ሁንዴና **ባለቤታቸው** ለአካባቢ ጥበቃ ልዩ ትኩረት ይሰጣሉ። በዚህም የተነሳ **በአካባቢያቸው** አስከፊ ድርቅ ተከስቶ አያውቅም። ረሃብና አካባቢን ጥሎ መሰደድም አልታየም። ይህም በመሆኑ የአካባቢው ህብረተሰብ ኑሮውን በተረጋጋ ሁኔታ እንዲመራ ምቹ አጋጣሚ **ፈጥረውለታል**። ስለዚህ ሁላችንም ይህን መልካም ተሞክሮ ወስደን ሥራ ላይ በማዋል አካባቢያችንን መጠበቅ ይኖርብናል።

(ከአፋን ኦሮሞ የመማሪያ መፅሐፍ 4ኛ ክፍል ተተርጉሞና ለክፍል ደረጃው እንዲመጥን ተደርጎ የቀረበ)

**ክፍለጊዜ ስድስት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ባነበባችሁት መሠረት ተገቢውን መልስ በቃል ስጡ።

1. አቶ ሁንዴና ባለቤታቸው የአፈር እጥበትን የመከላከል ሥራ የሚሰሩት መቼ ነው?
2. ለአፈር መታጠብ በምክንያትነት የተጠቀሰው ሐሳብ በየትኛው አንቀፅ ላይ ይገኛል ?
3. አቶ ሁንዴ ለሚኖሩበት አካባቢ ህብረተሰብ ንፁህ አየርና በቂ ዝናብ ማግኘት ምክንያት የሆነው ምንድን ነው?
4. አቶ ሁንዴና ባለቤታቸው ለአካባቢ ጥበቃ በሚሰጡት ልዩ ትኩረት የተገኙት ጥቅሞች ምንድን ናቸው?
5. ‹‹ባለቤታቸው›› በሚለው ቃል ውስጥ ያለውን ቅጥያ ለይታችሁ አንብቡ።

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## መልመጃ ሦስት

በ "ሀ" ሥር ያሉት የምንባቡ አንቀጾች የሚያስተላልፉትን መልዕክት በ "ለ" ሥር ከቀረቡት ውስጥ በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አንቀጽ አንድ | ሀ. አፈር እንዳይታጠብ ስለሚሰሩ ስራዎች |
| 2. አንቀጽ ሁለት | ለ. የተፈጥሮ ሀብትን ስለመንከባከብ |
| 3. አንቀጽ ሦስት | ሐ. የአካባቢ ጥበቃ በመከናወኑ ስለተገኙ ጥቅሞች |
| | መ. ስለአካባቢ ጥበቃ |

ክፍለጊዜ ስምንት

## መልመጃ አራት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ከቀረቡት አማራጮች መካከል በመምረጥ መልሱ።

1. አቶ ሁንዴ አንድ ዛፍ ሲቆርጡ ስንት ችግኞችን ይተካሉ?

   ሀ. ምንም  ለ. አንድ  ሐ. ሁለት  መ. ሶስት

2. በእነአቶ ሁንዴ እና ወይዘሮ ሶሬቲ የአካባቢ ጥበቃ ስራ የተነሳ ሕብረተሰቡ በደስታ እንዲኖር ያስቻለው ምክንያት ምንድን ነው?

   ሀ. በቂ ዝናብ ማግኘቱ  ሐ. ለም አፈር ማግኘቱ

   ለ. ንጹህ አየር ማግኘቱ  መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

3. የተተከሉ ችግኞች እንዲፀድቁ ምን መደረግ አለበት?

   ሀ. ከከብቶች ንክኪ መጠበቅ  ሐ. ለጎርፍ ማጋለጥ

   ለ. ግድብ መስራት  መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

4. አፈር በጎርፍ እንዳይወሰድ ምን መደረግ አለበት?

   ሀ. ከብቶችን ለግጦሽ በብዛት ማሰማራት

   ለ. ዛፍ መትከል ማቆም

   ሐ. እርከን መስራት

   መ. ቁልቁል ማረስ

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

### መልመጃ አምስት

የሚከተሉትን ሀሳቦች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሀሰት" በማለት በቃል መልሱ።

1. የአፈርን እጥበት እርከን በመስራት መከላከል ይቻላል።
2. ወይዘሮ ሶሬቲ የማገዶ እንጨት የሚለቅሙት ደረቁንና እርጥቡን ሳይመርጡ ነው።
3. አቶ ሁንዴና ባለቤታቸው አካባቢያቸውን የሚንከባከቡት ለብቻቸው ነው።
4. አቶ ሁንዴ ከሚቆርጡት ዛፍ ይልቅ የሚተክሉት ችግኝ ቁጥሩ ይበልጣል።

## ክፍለጊዜ አስር

### መልመጃ ስድስት

በምድብ "ሀ" ሥር ከምንባቡ ለወጡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከምድብ "ለ" መርጣችሁ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሀብት | ሀ. መባረር |
| 2. መሰደድ | ለ. ተዋሃደ |
| 3. ልምላሜ | ሐ. የድንጋይ ካብ |
| 4. ተላበሰ | መ. ግንኙነት |
| 5. እርከን | ሠ. ንብረት |

6. ንክኪ

ረ. ድርቀት

ሰ. አረንጓዴነት

**ክፍለጊዜ አስራ አንድ**

**መልመጃ ሰባት**

ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ስለቀለም መዋቅርና ምዕላድ የተማራችሁትን በማስታወስ የሚከተሉትን ቃላት በምዕላድ ደረጃ በመነጠልና በማጣመር ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

| ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|
| 1. ችግኝ-ኦች-ም | ችግኞችም |
| 2. የ-ደረቅ-ኧ-ው-ን | የደረቀውን |
| 3. በ-ተሞል-ኣ-በ-ት | በተሞላበት |
| 4. ህብረት- ኧ- ሰብ-ኡ | ህብረተሰቡ |
| 5. አካባቢ-ይ-ኣችን-ን | አካባቢያችንን |

## ትምህርት አራት፡መፃፍ

በዚህ ትምህርት ሥር የአንቀፅ ኃይለቃል ለይታችሁ ትፅፋላችሁ፤ ሆሄያትን በትክክል በመሰደር ቃላት ትፅፋላችሁ፤ ድምፀት አመላካቾችን በዓረፍተነገር ውስጥ ትጠቀማላችሁ።

**ክፍለጊዜ አስራ ሁለት**

**ተግባር አራት**

ሀ. ካሁን በፊት በምዕራፍ አንድ ስር በአንቀፅ ውስጥ ስለሚገኙ ዓረፍተነገሮች መማራችሁ ይታወሳል። በዚህም መሠረት “አካባቢ

ጥበቃ" በሚለው ፅሑፍ ውስጥ ያሉትን የአንቀፅ አንድ፣ ሁለትና ሶስት ኃይለቃሎች ለይታችሁ ፃፉ።

ለ. ከዚህ በታች ከቀረበው አንቀጽ ውስጥ ሃይለቃል እና ዘርዛሪ ዓረፍተነገሮችን ለይታችሁ አመልክቱ።

ችግኞች እንደቦታው ሁኔታ በመስመር ወይም ያለመስመር በአመቺ ቦታ ላይ ይተከላሉ። ቦታው አመቺ ከሆነ የመስመር አተካከልን መምረጥ የተሻለ ይሆናል። በአብዛኛው ለተከላ የምንጠቀመው ቦታ ሁሉም ጎኖች እኩል የሆኑ አራት ማዕዘናዊ መስመር አተካከል ዘዴ ነው። በተጨማሪም ሁለቱ ጎኖች እኩል የሆኑ ሶስት ማዕዘናዊና ስድስት ማዕዘናዊ አተካከልን መጠቀም ይቻላል። ችግኞችን በመስመር መትከል ወደፊት ለመንከባከብ የሚደረገውን ጥረት ቀላል ያደርጋል።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

**ተግባር አምስት**

**ለ. መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት ሆሄያቸውን በትክክል በመሰደር በደብተራችሁ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

**መልመጃ ስምንት**

**ሐ. የሚከተሉትን ድምፀት አመላካች ቃላት በዓረፍተነገር ውስጥ አስገብታችሁ አሳዩ። ተገቢ የሆኑትን ሥርዓተነጥቦች ለመጠቀም ሞክሩ።**

| | | |
|---|---|---|
| እሰይ | እግዚኦ | ወይኔ |
| ጎሽ | ዘራፍ | ወይጉድ |

ምሳሌ፡ አቤት! ምን ያህላል!

ክፍለጊዜ አስራ አራት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

**በቃላት ትምህርት ሥር ለቃላት መዝገበቃላዊ ፍች ትሰጣላችሁ፤ በፅሁፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት እያደናችሁ ታሳያላችሁ።**

### መልመጃ ሰባት

ከዚህ በታች ያሉት ቃላት ቀደም ሲል ስለአካባቢ ጥበቃ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ፍች ግለፁ።

1. መነመነ
2. ታጥቦ
3. ለም
4. ቁሳቁስ
5. ይተካሉ
6. እርከን
7. ጠባይ
8. ለቆ
9. ተላበሰ

ክፍለጊዜ አስራ አምስት

### መልመጃ ስምንት

በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡት ሀሳቦች ምንባቡ ውስጥ ባሉት አንድ አንድ ቃል የተወከሉ ናቸው። በዚህም መሠረት ቃሎቹን በማሰስ ለይታችሁ አውጡና አመልክቱ።

| ሐሳቦች | መልስ |
|---|---|
| 1. የምግብ ማብሰያ ወይም መቀቀያ | ማገዶ |
| 2. የቀለም ዓይነት | |
| 3. ለም አፈር በጎርፍ እንዳይታጠብ የሚሰራ | |
| 4. በክረምት ወራት የሚተከሉ | |
| 5. የዝናብ እጦት የሚያስከትለው | |
| 6. ከተግባር፣ ከልምድ የተገኘ ዕውቀት | |

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በሰዋስው ትምህርት ሥር ነጠላ ቁጥርና ብዙ ቁጥር ያላቸውን ስሞች ለይታችሁ ትፅፋላችሁ።

**ክፍለጊዜ አስራ ስድስት**

**ማስታወሻ**

**ነጠላና ብዙ ቁጥር ስሞች**

ነጠላ ቁጥር ስም፡ አንድ ብቻ የሆነን ስም የሚያመለክት ነው።

ብዙ ቁጥር ስም፡ ከአንድ በላይ የሆነ ስም የሚያመለክት ነው።

| ምሳሌ፡ | **የነጠላ ቁጥር ስም** | **የብዙ ቁጥር ስም** |
|---|---|---|
| | ልጅ | ልጆች |
| | በሬ | በሬዎች |
| | ቃል | ቃሎች/ቃላት |

## መልመጃ ዘጠኝ

ሀ. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ነጠላ ቁጥር ስሞችና ብዙ ቁጥር ስሞች ከስራቸው በማስመር ለይታችሁ አመልክቱ። በአንድ ዓረፍተነገር ውስጥ ከአንድ በላይ ስሞች ሊኖሩ ይችላሉ።

ምሳሌ፡ **ደኖች** ለዝናብ መኖር ምክንያት ናቸው።

1. የተተከሉ ችግኞች እንዲፀድቁ መንከባከብ ያስፈልጋል።
2. ታታሪ ገበሬ ችግኝ ይተክላል።
3. በሐምሌና በነሐሴ ወራት ኃይለኛ ዝናብ ይጥላል።

4. ከብቶች ዕፅዋት ያበላሻሉ።

5. ደን ከተጨፈጨፈ የዱር እንስሳት ይሰደዳሉ።

ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

## መልመጃ አስር

ለ. ለሚከተሉት የነጠላ ቁጥር ስሞች የብዙ ቁጥር ስሞቻቸውን ፃፉ።ምሳሌ፡ ፍየል- ፍየሎች

| ተራ ቁ. | ነጠላ ቁጥር ስም | የብዙ ቁጥር ስም |
|---|---|---|
| 1. | ዛፍ | |
| 2. | መፅሐፍ | |
| 3. | ቦታ | |
| 4. | ከብት | |
| 5. | ሀገር | |

ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

## መልመጃ አስራ አንድ

ሐ. ለሚከተሉት የብዙ ቁጥር ስሞች ነጠላ ቁጥር ስሞቻቸውን ፃፉ።

ምሳሌ፡ እንስሳት - እንስሳ

| ተራ ቁ. | የብዙ ቁጥር ስም | የነጠላ ቁጥር ስም |
|---|---|---|
| 1. | አካባቢዎች | |
| 2. | ቃላት | |
| 3. | ችግሮች | |
| 4. | መምህራን | |
| 5. | ሐረጋት | |

# ምዕራፍ ስድስት፡
# አደንዛዥ ዕጾችና ንጥረነገሮች

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**


- አደገኛ ዕጾችን ማስወገጃ መንገዶችን በተመለከተ አዳምጣችሁ ትረዳላችሁ፤
- የቀረበላችሁን ጽሁፍ አውድ ትተነብያላችሁ፤
- አንድን ጽሁፍ ለመረዳት ምልክቶችን፣ መግለጫዎችንና ወካዮችን ታነባላችሁ፤
- የዓረፍተነገር መሸጋገሪያዎችን ትገነዘባላችሁ፤
- ቃላትን ታጎለብታላችሁ፤ ፍቻቸውን ትናገራላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ስር አዳምጣችሁ እንድትረዱ የሚያግዙ ጽሑፍ፣ መልመጃና ተግባሮች ቀርበዋል። በመሆኑም በተሰጣችሁ ትዕዛዝ መሰረት ስሩ።

# ትምባሆ ማጨስ



## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ከላይ ከቀረበው ምስል የተረዳችሁትን ተናገሩ።
2. በአካባቢያችሁ ሱስ ያስይዛሉ ተብለው የሚታወቁ ዕጾች ምን ምን ናቸው?
3. እንደትምባሆና ጫት ያሉ ዕጾች እንዴት ጉዳት ያደርሳሉ?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች እያዳመጣችሁ በጽሑፍ መልሱ።

1. በትምባሆ ውስጥ የሚገኙት ንጥረነገሮች_________፣ _________እና _______ ናቸው።
2. ትምባሆ በጤና ላይ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች_______፣ _______፣ _________፣ ______እና ______ ናቸው።

ክፍለጊዜ ሁለት

# የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት ጽሑፍ መሰረት በቃል መልሱ።**

1. ትምባሆ ሱስ የሚያስይዘው እንዴት ነው?
2. በትምባሆ ውስጥ የሚገኙት ጎጂ ኬሚካሎች ወደሰው አካላት የሚገቡት ምን ሲሆን ነው?
3. የኒኮቲንን፣ የካርቦን ሞኖኦክሳይድን እና የታርን አንድነትና ልዩነት አብራሩ።

ክፍለጊዜ ሶስት

**ተግባር አንድ**

ቀጥሎ ያሉትን ተግባራት በቡድናችሁ ከተወያያችሁባቸው በኋላ በተወካችሁ አማካኝነት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

1. ትምባሆ ለሰውነት ጎጂ መሆኑ እየታወቀ በብዙ ሰው የሚጨሰው ለምንድነው?
2. በአደንዛዥ ዕጾች የሚከሰቱትን ጉዳቶች መከላከል አስፈላጊ የሆነው ለምን ይመስላችኋል?

## ክፍለጊዜ አራት

### መልመጃ ሁለት

ሀ. በአዳመጣችሁት ጽሑፍ መሰረት ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍች በጽሑፍ ስጡ።

1. ያቃውሳል
2. እንዲያመነጭ
3. ምት
4. በሚጨስ
5. ሱስ
6. ማስያዝ
7. እጾች
8. ንጥረነገሮች

ለ. በመቀጠል በምዕራፍ ሁለት ስለቀለም የተማራችሁትን በማስታወስ ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት በቀለም ከፋፍላችሁ አሳዩ።

1. ጎጇ
2. አሳ
3. አፍ
4. መንገድ
5. መንግስት
6. አበባ
7. ልብስ

## ክፍለጊዜ አምስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ከዚህ በታች በሱስ አስያዥ ጉዳዮች ዙሪያ እንድትናገሩ የሚያግዝ ተግባር ስለቀረበላችሁ በትዕዛዙ መሰረት ስሩ።

**ተግባር ሁለት**

ሀ. እንደትምባሆ ሁሉ ቡና እና ሻይ ሱስ እንደሚያሲዙ ይታወቃል። በመሆኑም በነዚህ ውስጥ ያሉ ንጥረነገሮችን ምንነታቸውን እና ጉዳታቸውን ከተለያዩ ምንጮች መረጃ በማሰባሰብ የቃል ዘገባ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ለ. በአካባቢያችሁ እንደልማድ ተደርገው ለመዝናኛነት ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉ ዕፅዋት ካሉ ጉዳታቸውን አስረዱ።

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

**ክፍለጊዜ ስድስት**

በዚህ ትምህርት ሥር ምንባብ ቀርቦላችኋል። ምንባቡን እያነበባችሁ የአንቀጾቹን ዋና ዋና ሀሳቦች ማስታወሻ ትይዛላችሁ። ከዚያም ከምንባቡ ለወጡ የተለያዩ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ትሰጣላችሁ።

## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ስጡ።

1. ጫት የሚመረተው ለምን ይመስላችኋል?
2. ስለጫት ጥቅምና ጉዳት ምን የሰማችሁት ነገር አለ?



## ጫት

ጫት ሱስ ከሚያስይዙ ዕጽዋት አንዱና በአገራችን በስፋት የሚመረት ነው። እንደገቢ ምንጭ ሆኖ ስለሚያገለግል ከጓሮ ጀምሮ በሰፋፊ ማሳዎች ላይ ይመረታል። ጫት በውስጡ በሚገኙ ንጥረነገሮች ምክንያት ሱስ የማስያዝ ከፍተኛ አቅም አለው። ተጠቃሚዎቹ ለየብቻም ሆነ በቡድን ይቅማሉ።

ጫት ለአገራችን ገበሬዎች ከፍተኛ የገቢ ምንጭ በመሆኑ በዚህ ረገድ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። በአንጻሩ ደግሞ ሱስ አስያዥ በመሆኑ የሚያደርሰውም ጉዳት ከፍ ያለ ነው። በተለምዶ ጫት የሚቃመው በቤት ውስጥ ወይም ገለል ባሉ ቦታዎች በቡድን በጨዋታ ታጅቦ በመሆኑ የሥራ ጊዜን ያባክናል። አምራቹ ሲቅም የሥራ ጊዜውን ከማባከን አልፎ ማግኘት የነበረበትን ገቢም

ይቀንስበታል። ሌሎች ቃሚዎችም ቢሆኑ ለሌሎች ጠቃሚ ጉዳዮች ሊውል የሚችለውን ገንዘብ ማባከናቸው ግልጽ ነው።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስካሁን ካነበባችሁት ምን ተረዳችሁ?
2. በቀጣይ የምታነቧቸው አንቀጾች ስለምን የሚያወሱ ይመስላችኋል?

ጫት ጉዳት እንዳለው እየታወቀ ጥቅም ብቻ እንዳለው አድርገው የሚወስዱ ወገኖች አሉ። እነዚህ ወገኖች ለጫት ጠቃሚነት እንደዋና ምክንያት የሚያቀርቡት የገቢ ምንጭ መሆኑንና አዝናኝነቱን ነው። በእርግጥ የጫት አምራቾች ጫትን ተክለው ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ለምርት ያደርሳሉ። ምርቱንም ገበያ ላይ በማዋል ገቢያቸውን ያሳድጉበታል። ምርቱ ከተነሳ በኋላም ተክሉ የማቆጥቆጥ ባህርይ ስላለው የተሻለ ምርት እያስገኘ ይሄዳል። በዚህ መልክ ምርቱ እየጨመረ መሄዱ አምራቹን የተሻለ ኑሮ እንዲኖር ሊያደርግ ይችላል።

በአንጻሩ ደግሞ የጫት ተጠቃሚ እየበዛ መሄድ የሱሰኞች ቁጥር እየጨመረ እንዲሄድ ያደርጋል። እነዚህም ሰዎች ለሥራ ከመትጋት ይልቅ ሱሳቸውን ለማርካት ጊዜያቸውን ያለአግባብ እንዲያባክኑ ያደርጋል። ይህ ደግሞ የሰዎችን የማምረት አቅም በመቀነስ ለድህነት ይዳርጋል፤ ለጤናም ጠንቅ ይሆናል። በተለይም ነፍሰጡር ሴቶች ጫት ሲቅሙ በሽሉ እድገት ላይ ያለው ተጽእኖ የከፋ ይሆናል። ጡት ሲያጠቡም የጫቱ አነቃቂ

ንጥረነገሮች በእናት ጡት በኩል ወደህጻኑ በመግባት በህጻኑ እድገት ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ። የስኳር በሽታና የደም ግፊት ያለባቸው ሰዎች የሚወሰዷቸውን መድኃኒቶችንም ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል።

(ከተለያዩ ጽሁፎች ሀሳብ ተወስዶ ለክፍሉ ትምህርት እንዲስማማ ተደርጎ የተዘጋጀ)

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## መልመጃ ሶስት

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆኑ መልሶችን በቃል ሰጡ።**

1. የጫትን ጉዳት እና ጥቅም ግለጹ።
2. ጫት የሚመረተው በአብዛኛው ለምን ዓላማ ነው?
3. ቃሚዎች በቡድን ሆነው የሚቅሙት ለምን ይመስላችኋል?
4. ‹‹የጫት ተክል የማቆጥቆጥ ባህርይ አለው›› ሲባል ምን ለመግለጽ ታስቦ ይመስላችኋል?

**ክፍለጊዜ ስምንት**

**ለ. በምንባቡ መሰረት ቀጥሎ የቀረቡት ሀሳቦች ትክክል ከሆኑ “እውነት” ትክክል ካልሆኑ ‹‹ሐሰት›› በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያቱን አስረዱ።**

1. ጫት ሱስ ማስያዝ የሚችለው ሲታይ ማራኪ በመሆኑ ነው።
2. እንደአንዳንዶቹ ሃሳብ ጫት ሰዎችን የማዝናናት አቅም አለው።

3. የጫት ምርት ቢታገድ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚደርስ ተጽእኖ ሊኖር አይችልም።
4. የጫት ተጠቃሚ ቁጥር እየበዛ መሄድ ለሱሰኞች መብዛት ምክንያት ይሆናል።
5. ጫትን መጠቀም ድብርትን ለዘለቄታው ሊያስወግድ መቻሉ በጥናት ተረጋግጧል።

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

ቀጥሎ የመፃፍ ክሂላችሁን እንድታዳብሩ የሚያግዙ ተግባሮችና መልመጃ ስለቀረበ በተሰጣችሁ ትዕዛዞች መሰረት ስሩ።

**ተግባር ሶስት**

**ሀ. በቡድን በመሆን በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በማስታወሻችሁ ላይ ፃፉ።**

- ሱስ የሚያስይዙ እጾች የሚመሳሰሉባቸውና የሚለያዩባቸው ነጥቦች ምን ምን ናቸው?
- የቡና እና የሻይ ሱስ ከጫትና ከትምባሆ ሱስ በምን ይለያል?

ክፍለጊዜ አስር

**ለ. ቀጥሎ በቀረቡት መነሻ ሀሳቦች ላይ ተመስርታችሁ አጫጭር ጽሑፎችን አዘጋጁና ለመምህራችሁ አሳዩ።**

1. ሱሰኛ መሆን በማሕበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያሳጣል።

2. የቡና ሱስ ከጫት ሱስ የተሻለ ነው።
3. "ማንኛውም ሰው ከሱስ ነጻ አይደለም" የሚለው ሀሳብ የተሳሳተ እንደሆነ የሚያምኑ ወገኖች አሉ። ሀሳቡን በመቃወም ወይም በመደገፍ ፃፉ።

**ክፍለጊዜ አስራ አንድ**

## መልመጃ አራት

**ቀጥሎ ባለው አንቀጽ ውስጥ የሚገኙ መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋት ለይታችሁ ፃፉ።**

ጫት መቃም ለብዙ ሰዎች ምቾት ካለመስጠቱም በላይ አካላዊና ስነልቦናዊ ችግሮችን ያስከትላል። ይህም የስሜት መለዋወጥን ያመጣል፣ የደም ግፊትን ይጨምራል፣ ሥርዓትአተነፋፈስን ያፋጥናል። በተጨማሪም አላስፈላጊና መቋጫ የሌለው ወሬን ለማውራት ያነሳሳል። ከዚህም በሻገር ለብዙ ዓይነት ያልተለመዱና ቅቡልነት ለሌላቸው ባህሪያት ያጋልጣል። በተለይም በወጣቶች ላይ የደም ግፊትን ሊያመጣ ይችላል። እንዲሁም ከፍተኛ የራስ ምታትን፣ የደም ወደጭንቅላት መፍሰስን፣ የልብ በሽታን፣ የሳንባ ችግሮችንና የጉበት መበላሸትን ሊያስከትል ይችላል።

**ክፍለጊዜ አስራ ሁለት**

### ተግባር አራት

**ቀጥሎ ያለውን ኃይለቃል የሚዘረዝሩ ዓረፍተነገሮችን በመሸጋገሪያ ሐረጎች ተጠቅማችሁ በማያያዝ አንድ አንቀጽ ጻፉ።**

እንጀራን ለመጋገር ልንከተላቸው የሚገቡ ሂደቶች አሉ። በመጀመሪያ …በመቀጠል…ከዚያም…በመጨረሻም…።

ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ቃለትን በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን የምንመሰርትበት፤ ለተለያዩ ቃላት አውዳዊ ፍች እንድትሰጡ የሚያስችላችሁ ተግባሮች ስለቀረቡ በትኩረት ስሩ።

### መልመጃ አምስት

**ሀ. ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት ዓረፍተነገሮች መስርቱ።**

1. መቃም
2. ሱስ
3. ባህርይ
4. ዕፀዋት
5. ማቆጥቆጥ
6. ማባከን
7. ማጎልበት
8. ቀረጥ
9. አዘቅት
10. ተመጽዋች

ክፍለጊዜ አስራ አራት

**ለ. ከሚከተሉት ቃላት መርጣችሁ በክፍት ቦታዎቹ ውስጥ በማስገባት አንቀጹን አሟሉ።**

| | | |
|---|---|---|
| ቢፌስ | ጥርግራጊ | ከቆሻሻ |
| ቅር | መውረጃ | |
| ጤንነት | ፍሳሽ | |

አካባቢን———— መጠበቅ የራስን———— መጠበቅ የማይመስላቸው ብዙ ሰዎች አሉ። አንዳንዶች የግቢያቸውን ——

——— ሰብስበው ከአጥራቸው ውጪ ባገኙት ቦታ ይጥላሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ በውሀ ———— ቦዮችና በመንገድ ዳር ለመድፋት———— አይላቸውም። የልብስ እጣቢ ———— ከቦይ ወጥቶ አስፋልት ላይ ———— ፣ የእግር መንገድ ቢጨቀይ፣ ጎድጓዳ ስፍራ ቢጠራቀም ግድ የማይሰጣቸው አሉ።

ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ስር የቃል ክፍላቸው ስምና ግስ የሆኑትን በዓረፍተነገር ውስጥ እንድትጠቀሙ የሚያስችሏችሁ መልመጃዎች ቀርበዋል። ስለሆነም ጥያቄዎቹን በተሰጣችሁ ትዕዛዞች መሰረት በትኩረት ስሩ።

**ማስታወሻ**

ስም ማለት የሰው፣ የእንሰሳት እና የነገሮች መጠሪያን የሚገልጽ ነው።

ምሳሌ፡ ቶላ ፣ ግርማ ፤ አንበሳ፣ ዛፍ፣ ቤት

ግስ ማለት ድርጊትን፣ መሆንና እና መኖርን የሚገልጽ ነው።

ምሳሌ፡ ጠረገ፣ ነው፣ አለ

### መልመጃ ስድስት

ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ስም ወይም ግስ በማለት ለይታችሁ መድቡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ልብስ | ወረቀት | ወንበር |
| በላ | ጎበኘ | ሰጠ |

| | | |
|---|---|---|
| አጠና | ገበረ | ገመዳ |
| ገዛ | መጽሀፍ | ጨረቃ |

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

ከታች ባለው ምሳሌ መሠረት በአንቀጹ ውስጥ ያሉትን ስሞችና ግሶች ለዩ። ከዚያም በቃላቱ ዓረፍተነገሮች መስርቱ።

ምሳሌ፡ ወተት (ስም)፣ ያልፋል(ግስ)

ዓረፍተነገር፡ ለማህበረሰቡ ከፋብሪካዎች የሚቀርበው ወተት ብዙ ሂደቶችን ያልፋል።

የሸላ ወተት ፋብሪካ የሚሸጠው ወተት ህዝብ ዘንድ ከመድረሱ በፊት ብዙ ሂደቶችን ያልፋል። በመጀመሪያ ወተቱ በፋብሪካው ውስጥ ካሉ ላሞችና በአዲስ አበባና በዙሪያዋ ከሚገኙ ገበሬዎች ይሰበሰባል። ይህ የተሰበሰበው ወተት በትላልቅ የብረት ጋኖች ተሞልቶ ለፋብሪካው ይቀርባል። ከዚያም ፋብሪካው ተቀብሎ ወደ ማፍያ ጋን ውስጥ ይገለብጣል። ቀጥሎም በተወሰነ የሙቀት ልኬት ውስጥ በማፍላት ክሬሙ እንዲለይ ይደረጋል። በመጨረሻም ወተቱ ታሽጎ ለገበያ ያቀርባል።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ ሰባት

ሀ. በሳጥን ውስጥ የቀረቡትን ስሞች ተጠቅማችሁ የተጓደሉ ዓረፍተነገሮችን አሟሉ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ዝሆን | መጽሐፍ | አምፖል | ደን | ዴዴሳ | ኮምፒውተር |

1. ጓደኛዬ ——— ቀዶ መለሰልኝ።
2. ——— የዱር እንሰሳ ነው።
3. ——— የሰውን ልጅ ስራ የሚያቀል ዘመናዊ የኤሌክትሮኒስ መሳሪያ ነው።
4. የአባይ ትልቁ ገባር ወንዝ——— ነው።
5. የገዛሁት 60 ሻማ——— ተቃጠለ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

ለ. የሚከተሉትን የተጓደሉ ዓረፍተነገሮች በተገቢ ግሶች አሟሉ።

1. ኑሮ በጣም____________________።
2. እህቴ የኮሮና መከላከያ__________________።
3. ወታደሩ ወደ ጦር ሜዳ__________________።
4. ነጋዴዎቹ የተጨማሪ እሴት ታክስ_______።
5. ተማሪዎቹ በዘመቻ ችግኝ_____________ ።

# ምዕራፍ ሰባት፡ ምግብ

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- በሚደመጠው ነገር ውስጥ የሚገኙ ሀሳቦችን ታወዳድራላችሁ፣ ታነጻጽራላችሁ፣
- ስርዓተነጥቦችን ለይታችሁ ትጠቀማላችሁ፣
- ሒደታዊ ትንተና አንቀጽን ታነባላችሁ፣ ትጽፋላችሁ፣
- የቃላትን መዝገበቃላዊ ፍች ትሰጣላችሁ፣
- የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ስሞችን በመለየት ትጠቀማላችሁ፣
- ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን ለማንበብ የምዕላዳዊ ትርጉም እውቀታችሁን ትጠቀማላችሁ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ስር "ውኃ" በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሁፍን ታዳምጣላችሁ። አዳምጣችሁም የቀረበውን መልመጃና ተግባር በትእዛዞቹ መሰረት ትሰራላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

### ውኃ

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በቀን ስንት ብርጭቆ ውኃ እንደምትጠጡ ለክፍል

ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

2. በቂ ውኃ መጠጣት ምን ጥቅም አለው ትላላችሁ?
3. "እንሽርሽሪት" የሚለውን ቃል ፍች ገምቱ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አምስት የውኃ ጥቅሞችን ዘርዝሩ።
2. ምግብ ሳይበላ ሲቆይ የሚከሰት የአፍ ጠረንን በምን መከላከል ይቻላል?

ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት መሰረት በቃል መልሱ።**

1. እያንዳንዱ ሰው በቀን ምን ያህል ውኃ መጠጣት አለበት?
2. የምግብ እንሽርሽሪት የሚቀላጠፍበት ሂደት በውኃ ባይስተካከል ምን ችግር ሊፈጠር ይችላል?
3. በአዳመጣችሁት ጽሑፍ ውስጥ “ሆኖም፣ እንዲያውም፣ በመሆኑም፣ በተጨማሪም እና ከዚህም ሌላ” የሚሉ ቃላትና ሐረጋት ጥቅም ላይ ውለዋል። በመሆኑም እነዚህ ቃላትና ሐረጋት ምን በመባል ይታወቃሉ ? አገልግሎታቸውስ ምንድን ነው?

ክፍለጊዜ ሶስት

## መልመጃ ሁለት

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት ጽሑፍ መሰረት ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. የደማችን ሥርዓት ዝውውር የተቀላጠፈ የሚሆነው በምን ምክንያት ነው?

   ሀ. በምግብ ስልቀጣ ሰበብ    ሐ. በቂ ውኃ በመጠጣት

   ለ. አብዛኛው ክፍል ውኃ በመሆኑ    መ. ምግብን አልሞ በመዋጥ

2. በአንዳንድ ምግቦች ውስጥ የሚገኙት ንጥረነገሮች ከሰውነት ውስጥ ማስወገድ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

   ሀ. ክምችታቸውን ለመቀነስ

   ለ. ሰውነታችንን ስለሚጎዱ

   ሐ. ተፈላጊ ስላልሆኑ

   መ. መርዛምነታቸውን ለመቀነስ

3. ከሚከተሉት ሐሳቦች ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ውኃ ለምግብ ስልቀጣ እምብዛም አስፈላጊ አይደለም።

   ለ. በአንዳንድ ምግቦች ውስጥ መርዛማ ባህርይ ያላቸው ንጥረ ነገሮች አሉ።

   ሐ. ውኃ ከምግብ ክፍሎች አንዱ ነው።

   መ. ውኃ መጠጣት ለውፍረት ምክንያት ሊሆን አይችልም።

4. የውኃ ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ቁመት እንዳይጨምር መቆጣጠር

ለ. የደም ዝውውርን ማቀላጠፍ

ሐ. ጎጂ ንጥረነገሮችን ማስወገድ

መ. የቆዳን ውበት መጠበቅ

ክፍለጊዜ አራት

**ለ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ሃሳቦች በምሳሌው መሰረት በማወዳደርና በማነጻጸር ግለጹ።**

ምሳሌ፡ ኮምፒውተር እና የጽህፈት መኪና
ኮምፒውተር እና የጽህፈት መኪና ሁለቱም ለመጻፍ ያገለግላሉ። (ማወዳደር)

ኮምፒውተር ከጽህፈት ስራ ውጪ በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን የጽህፈት መኪና ግን ለጽህፈት ተግባር ብቻ ያገለግላል። (ማነጻጸር)

1. ክረምት እና በጋ
2. የቤት እንስሳት እና የዱር እንስሳት
3. ውሃ መጠጣት እና አለመጠጣት
4. የየብስ እና የአየር መጓጓዣ

ክፍለጊዜ አምስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ስር የመናገር ክሂላችሁን እንድታዳብሩ የሚያግዙ የተለያዩ ተግባሮች እና ማስታወሻ የቀረበላችሁ ስለሆነ በትዕዛዞቹ መሰረት ስሩ።

ተግባር አንድ

የምግብ ባለሙያን ወይም ሌላ ሰው ስለውኃ ጠቀሜታ ጠይቃችሁ ያገኛችሁትን መልስ ተራ በተራ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

### ተግባር ሁለት

ቀጥሎ በተሰጠው ማስታወሻ ላይ ተመስርታችሁ በቡድናችሁ በመሆን የምግብ ጠቀሜታ በሚል ርዕስ ሐሳብ ተለዋወጡ። ከዚያም የተስማማችሁበትን በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ተማሪዎች በንግግር አቅርቡ።

### ማስታወሻ

በንግግር ጊዜ ትኩረት ልታደርጉባቸው የሚገቡ ነጥቦች፡-

1. ንግግር የምታደርጉበትን ርዕሰጉዳይ ማወቅ፣
2. ርዕሰጉዳዩ ከያዛቸው ነጥቦች ውስጥ የበለጠ ጠቃሚ ነው የምትሉትን አሳጥራችሁ መያዝ፣
3. ነጥቦቹን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣
4. የአድማጮችን ችሎታ መገመት፣
5. ግልጽ የሆኑ ቃላትን ተጠቅሞ መናገር፣
6. የአድማጮችን ትኩረት እየተከታተሉ መናገር፣

**ክፍለጊዜ ሰባት**

**ተግባር ሶስት**

**ሀ. ቀጥሎ በቀረቡት መነሻ ሀሳቦች ላይ ተመስርታችሁ በቃል ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተራ በተራ ተናገሩ።**

1. ውኃ የመጠጣት ጠቀሜታ
2. ወተት መጠጣት የሚያዘወትሩ ሰዎች በቂ ውኃ መጠጣት የሚያስፈልጋቸው ለምን እንደሆነ

**ክፍለጊዜ ስምንት**

**ተግባር አራት**

**የውኃ አጠቃቀምን በተመለከተ በቡድናችሁ ተወያዩና የደረሳችሁበትን በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።**

**ማስታወሻ**

- ውይይት ስታደርጉ አንድ አወያይ ሊኖራችሁ ይገባል።
- በመወያያ ርዕሳችሁ ላይ ሀሳብ የምትሰጡት አወያዩን አስፈቅዳችሁ መሆኑን ማወቅ ይጠበቅባችኋል።
- በዛ ያሉ ሀሳቦች እንዲንሸራሸሩ ሀሳባችሁን አጠር አድርጋችሁ አቅርቡ።
- አንዱ የተናገረውን ሀሳብ መድገም ጥቅም ስለሌለው በአዲስና መቅረት በሌለበት ነጥብ ላይ አትኩሩ።
- ሌላው ሀሳብ ሲሰጥ ጥሩ አድማጭ ሁኑ።



ዘመናዊ ምግቦች በከፊል



የባህል ምግቦች በከፊል

## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. ከላይ ካሉት ምስሎች ምን ተረዳችሁ?
2. አንድ ሰው በቂ ምግብ ካላገኘ ምን ጉዳት ይገጥመዋል?
3. የተመጣጠነ ምግብ ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

## ምግብ

በሌላው ዓለም በቤት ውስጥ የሚዘጋጁ ምግቦችን መመገብ የሥልጣኔና የጤንነት ምልክት ተደርጎ መታሰብ ከጀመረ ዋል አደር ብሏል። በሀገራችን እምብዛም ግምት የማንሰጣቸው ቢሆኑም የተለያዩ ምግቦች በብዛት ይገኛሉ። ከነዚህም ውስጥ የተጠበሰ በቆሎ፣ ቆሎ፣ ንፍሮና የመሳሰሉትን መብላት የተለመደ ነው። እነዚህ ምግቦች ብዛት ያላቸውን የተለያዩ ንጥረነገሮች ይዘዋል።

በቤት ውስጥ የሚዘጋጁ ምግቦች ከአሰራር ቅለትና ከወጪ አንጻር የተሻሉ ናቸው። ለምሳሌ ድንች እንደልብ በሚገኝበት አገር በቀላሉ ገዝቶና ቀቅሎ መብላት ሲቻል አንዳንዶቹ የታሸገ ድንች ጥብስ ከሱቅ ገዝተው ሲበሉ እናያለን። በውድ ዋጋ ገዝተን ከምንበላው የታሸገ የድንች ጥብስ ይልቅ፣ በቤታችን የምናዘጋጀው የድንች ቅቅል የተሻለ ነው። ቡላ እና የገብስ ቂጣ እንደ ልብ በሚገኝባት አገር እየኖርን ልጆቻችንን በታሸገ ዱቄት መደለል አስገራሚ ነው። በአገራችን የሚመረተው የኑግ ዘይት ከዱባይ ከሚመጣው ይበልጥ መሻሉንም ማወቅ ተገቢ ነው።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. በአገራችን ________፣_______፣_____ እና የመሳሰሉትን መብላት የተለመደ ነው።
2. በአገራችን የሚመረተው_____ ከዱባይ ከሚመጣው ይበልጥ መሻሉን ማወቅ ተገቢ ነው።

ባህላዊ ምግቦችን አመጣጥነን፣ ለልጆች በሚጣፍጣቸውና በሚስባቸው መንገድ በማቅረብ እንዲመገቡ ማድረግ ይቻላል። ለምሳሌ የገብስ ቂጣ ለዓይን በሚያምር መልኩ ከተዘጋጀ ለተመጋቢው ጣፍጦ ይበላል። ከጤፍ ወይም ከስንዴ ቂጣ የሚዘጋጀው ጨጨብሳ ደግሞ ማጣፈጫ ተደርጎበት ከተሰራ ተመራጭና የተመጣጠነ ይሆናል። እንዲሁም በሥርዓት የተገነፋ የበቆሎ ገንፎ ለዓይን ከመሳቡም በላይ ጣፋጭና ለጤና ተስማሚ ምግብ ነው። ከዚህም ሌላ ከአጃ የሚሰራው አጥሚት ወይም ሾርባ የተጎዳን ሰውነት በመጠገን ተወዳዳሪ የለውም። በተለይ በጥሩ ሁኔታ የተቆላ የገብስ ቆሎ በቅቤ ወይም በመጠነኛ ዘይትና በበርበሬ ታሽቶ ሲቀርብ በፍቅር ይበላል። ከልዩ ልዩ እህሎች ከተፈጨ ዱቄት የሚዘጋጅ ጭብጦም ከተቻለ ቅቤ ቢጨመርበት የተሻለ ተመጣጣኝ ምግብ ይሆናል።

በሀገራችን የተመጣጠነ ንጥረነገር ያላቸው ሌሎች የምግብ ዓይነቶችም አሉ። ከነዚህም አንዱ ቆጮ ነው። ቆጮ ከእንሰት ተክል የሚዘጋጅ ምግብ ሲሆን በውስጡ ለሰውነት እጅግ ጠቃሚ

የሆኑ የተለያዩ ንጥረነገሮችን የያዘ ነው። እንዲሁም ከልዩ ልዩ የእህል ዘሮች ከሚዘጋጁ ማባያዎች ጋር የሚቀርበው እንጀራም ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ምግብ ነው። በመሆኑም እንጀራ የተመጣጠነ ንጥረነገር በማግኘት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።

በአጠቃላይ የተለያዩ የምግብ አይነቶች ይገኛሉ። እነዚህ ምግቦች ለሰውነት ግምባታም ሆነ ለጤና ጠቀሜታ ያላቸው ናቸው። ስለሆነም ምግቦቹን ለይቶ ከሌሎች ምግቦች ጋር ጎን ለጎን መመገብ ምግብን ለማመጣጠን ይረዳል። በመሆኑም በአገራችን በተለያዩ ስፍራዎች ያሉትን የምግብ አይነቶች አጥንተን፣ አንዱን ካንዱ ጋር እያዋሀድን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

(ኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ሰባተኛ ክፍል ተሻሽሎ የተወሰደ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሶስት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልሱ።**

1. በልዩ ልዩ የእህል ዘሮች ከሚዘጋጁ ማባያዎች ጋር ሲበላ ጠቀሜታ ያለው ምግብ ምንድነው?
2. ‹‹ የጤንነትና የስልጣኔ አመጋገብ… ›› ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. ‹‹ለዓይን የሚማርክ ምግብ›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

4. የተጎዳን ሰውነት በመጠገን ተወዳዳሪ የለውም የተባለው የትኛው የምግብ አይነት ነው?
5. በቤታችን የምናዘጋጀው የድንች ቅቅል የተሻለ ነው ተብሎ የተወዳደረው ከየትኛው የምግብ አይነት ጋር ነው?
6. በአንቀጽ አንድ፣ በአራተኛው አረፍተ ነገር ውስጥ "እነዚህ" የሚለው የሚገልጸው ምንን ነው?

## ክፍለጊዜ አስር

**ለ. የሚከተሉትን ሐሳቦች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" ካላችሁ በኋላ ምክንያቱንም ጻፉ።**

1. በአገራችን የተጠበሰ በቆሎ፣ ቆሎና ንፍሮ በቤት ውስጥ የሚዘጋጁ ምግቦች ናቸው።
2. በአገራችን ያሉ ምግቦች አስፈላጊ ንጥረነገሮችን የያዙ ናቸው።
3. ቆጮ ከእህል የሚዘጋጅ የምግብ አይነት ነው።
4. ምግቦችን ለያይቶ ጎን ለጎን መመገብ ምግብን የተመጣጠነ ያደርጋል።
5. በቤት ውስጥ የሚዘጋጁ ምግቦች ለአሰራር የማያስቸግሩና አነስተኛ ወጪ የሚጠይቁ ናቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

ሐ. ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ከምንባቡ በተረዳችሁት መሰረት የቀረቡትን ምግቦች ዘመናዊ ወይም ባህላዊ በማለት መድቡ።

| | |
|---|---|
| ገንፎ | ባህላዊ |
| የተወቀጠ ኑግ | |
| የዱባይ ዘይት | ዘመናዊ |
| የገብስ ቂጣ | |
| የባቄላ ንፍሮ | |
| ጨጨብሳ | |
| የታሸገ ዱቄት | |
| አጥሚት | |
| ጭብጦ | |
| የታሸገ የድንች ጥብስ | |
| የተቀቀለ ድንች | |
| እንጀራ | |

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

### ተግባር አምስት

በቤት ውስጥ በሚዘጋጅ ምግብና በፋብሪካ በሚመረት ምግብ መካከል ስላለ አንድነትና ልዩነት መረጃ በመሰብሰብ ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት ክፍል አንቀጾች እንድትጽፉ እና ስርዓተነጥቦችን በቦታቸው እንድትጠቀሙ የሚረዱ ተግባሮችና መልመጃዎች ቀርበዋል። ስለሆነም በትእዛዞቹ መሰረት ስሩ።

### ማስታወሻ

**ስርዓተነጥቦች**

ስርዓተነጥቦች አንድን ጽሁፍ በተገቢው መንገድ እንድናነብ ይረዱናል። የስርዓተነጥቦችን አጠቃቀም ማወቅ ስንጽፍ በተገቢው ቦታ አስገብተን አንባቢን ከማደናገር እናድናለን። ከነዚህም ስርዓተነጥቦች የተወሰኑት ቀጥለው ቀርበዋል።

1. አራት ነጥብ(።) በዓረፍተነገር መጨረሻ ላይ ይገባል። ምሳሌ፡ ገመቹ ጎበዝ ተማሪ ነው።
2. ነጠላ ሰረዝ(፣) በሚዘረዘሩ ነገሮች መሃል ይገባል። ምሳሌ፡የእህል አይነቶች ጤፍ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ስንዴና ወዘተ. ናቸው።

ጥያቄ ምልክት(?) ጥያቄያዊ ከሆኑ ወይም ምላሽ ከሚፈልጉ ዓረፍተነገሮች ቀጥሎ ይገባል። ምሳሌ፡ አገርህን ትወዳለህ?

## መልመጃ አራት

ማስታወሻውን መሠረት አድርጋችሁ ከዚህ በታች በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተጓደሉትን ስርዓተነጥቦች አሟሉ።

1. እናቴ ከገበያ ቲማቲም ቃሪያ ጎመን እና ሽንኩርት ገዛች
2. ዛሬ ከትምህርት ቤት የቀረው ማን ነው
3. ውጪ ሀገር የሄደችው እህቴ የእጅ ስልክ አልባሳት ገንዘብና ሽቶ ላከችልኝ
4. ከኮቪድ በሽታ ራሳችንን እንዴት እንከላከላለን

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

### ተግባር ስድስት

**ከዚህ በታች የቀረበውን ምሳሌ መሠረት አድርጋችሁ ከተሰጡት ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ አንቀጽ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

**ምሳሌ**

በቅድሚያ የታረደው ዶሮ ከታጠበ በኋላ ድስት ይጣድና ሽንኩርት ይጨመራል። ሽንኩርቱ የሞቀ ውሃ ጠብ እየተደረገበት አጋም እስኪመስል ይማሰላል። ከዚያም ዘይት እንዳያንስ ወይም እንዳይበዛ ተመጥኖ ሽንኩርቱ ላይ ይጨመራል። የማጣፈጫ ቅመሞችና የተመጠነ በርበሬ ይታከልና ሽንኩርቱ በደንብ እስኪበስል ድረስ ይቁላላል። በመቀጠልም የተበለተው ስጋ በቢላዋ

እየተከረከረ ድስቱ ውስጥ በመጨመር ይማሰላል። ከዚህ በኋላ ከግማሽ ጭልፋ ያላነሰ ቅቤና የማስተካካያ ቅመሞች ይጨመራሉ። በመጨረሻም ምጥኑ መስተካከሉ ይቀመስና ድስቱ እንደተጣደ በጋለው ምድጃ ላይ እንዲቆይ ይደረጋል። ይህም ወጡ እየተጨለፈ እስኪበላ ድረስ ቅባቱ እንዳይረጋ ያደርገዋል።

(ከ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ፣ 1990 ተሻሽሎ የተወሰደ።)

1. የቡና አፈላል
2. የገንፎ እህል አዘገጃጀት
3. የጠላ አጠማመቅ

**ክፍለጊዜ አስራ አምስት**


## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ስር ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን የምእላድ ትርጉሞቹን እውቀት ለመጠቀም የሚያስችሏችሁ መልመጃዎች ቀርበውላችኋል። በመሆኑም በተሰጣችሁ ትእዛዝ መሰረት ስሩ።

### መልመጃ አምስት

**ሀ. ቀጥሎ የቀረቡ ምእላዶችን (ቅጥያዎችን) ሊያስጡ የሚችሉ ቃላትን በምሳሌው መሰረት አፍልቁ።**

**ምሳሌ**



1. -ኣማ
2. -ኣም
3. -ኸኛ
4. -ነት
5. -ኢያ
6. -ኢ

ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት መዝገበቃላት በመጠቀም ፍቻቸውን ከሰጣችሁ በኋላ ዓረፍተነገር መስርቱባቸው።

| | | |
|---|---|---|
| ጭብጠ | ልጅ | ገንፎ |
| ዱቄት | ዘር | ስንዴ |
| ውሃ | ዘይት | ገበሬ |

ክፍለ ጊዜ አስራ ሰባት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ክፍል ስለሚቆጠሩና ስለማይቆጠሩ ስሞች ማስታወሻ ቀርቦላችኋል።መልመጃዎችና ተግባሮችም ተሰጥተዋል። በመሆኑም በቀረበላችሁ ትእዛዞች መሰረት ስሩ።

**ማስታወሻ**

ስም ለአንድ ነገር መጠሪያነት የሚውል ቃል ነው። ስሞች የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ።

**ምሳሌ፡** ሰው፣ በሬ፣ ብርጭቆ፣ ዛፍ፣ ወዘተ. የሚቆጠሩ ስሞች ሲሆኑ፣ ስኳር፣ አሸዋ፣ አፈር፣ ጤፍ ወዘተ. የማይቆጠሩ ስሞች ናቸው።

## መልመጃ ስድስት

ሀ. ቀጥሎ የቀረቡትን ስሞች የሚቆጠሩ ወይም የማይቆጠሩ በማለት መድቡ።

| | |
|---|---|
| አገር | |
| ዱቄት | |
| ልጅ | |
| ዘይት | |
| ገበሬ | |
| ውሃ | |

ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

ለ. የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ስሞችን አምስት አምስት ጻፉ።

# ምዕራፍ ስምንት፡ የዱር እንስሳት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- የተማራችሁትን ውስብስብ የቀለም መዋቅሮች እንዴት እንደምታጣምሩ አዳምጣችሁ ትረዳላችሁ፤
- ውስብስብ የቃላት መዋቅሮችን ታነባላችሁ፤
- አንቀጽን በማወዳደርና በማነጻጸር ተረድታችሁ ትጽፋላችሁ፤
- የሥነ-ምዕላዳዊ ፍች ዕውቀታችሁን ትጠቀማላችሁ፤
- ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን ትጠቀማላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ክፍል "ስጋ በል የዱር እንስሳት" የሚል የማዳመጥ ጽሁፍን በመጠቀም የቀረቡትን ተግባሮችና መልመጃዎች ስሩ።

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ስጋ በል የዱር እንስሳት ዘርዝሩ።
2. የእንስሳቱን ጉዳትና ጥቅም ምን እንደሆነ ግለፁ።

## የማዳመጥጊዜ ጥያቄዎች

1. ስጋ በል እንስሳት ብዙውን ጊዜ የሚታወቁት——— ነው።
2. ስጋ በል የዱር እንስሳት ከ——— እንስሳት ጋር ሲወዳደሩ በአብዛኛው በክብደትም ሆነ በመጠን ከፍተኛ ናቸው።
3. የስጋ በል የዱር እንስሳት ጠንካራ ጥፍራቸው ለ——— እና ለ——— ያገለግላቸዋል።

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ጽሁፍ መሰረት በቃል መልሱ።**

1. የአብዛኛዎቹ ስጋ በል እንስሳት መለያ ባህሪ ምንድነው?
2. ስጋ በል እንስሳት መብላት የሚፈልጉትን እንስሳ እንዴት አድርገው ይይዛሉ?
3. ስጋ በል እንስሳት ሰለባዎቻቸውን የመያዝ ችሎታ እንዴት አድርገው ያዳብራሉ?
4. ሀይለኛ የሚባሉት ስጋ በል እንስሳት ምን ምን ናቸው?
5. ‹‹ሰለባዎች ...›› ሲል ምን ማለት ነው?

## ክፍለጊዜ ሶስት

**ለ. ባዳመጣችሁት ጽሁፍ መሰረት ከዚህ በታች የቀረቡት ሀሳቦች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ።**

1. ስጋ በል እንስሳት ለሰው ልጆች ስጋት አይደሉም።
2. ስጋ በል እንስሳትን አናሳና ከፍተኛ በማለት ይከፈላሉ።
3. ስጋ በል እንስሳት ሰለባቸውን ሳይሞት በቁሙ ግጠው ስለሚጨርሱ ምድባቸው ምንጊዜም አውሬ ነው።
4. ስጋ በል እንስሳት እንደማንኛውም እንስሳ ይቆጠራሉ።
5. ከፍተኛ ስጋ በሎች በአብዛኛው ውሻ መሳይ ናቸው።

## ክፍለጊዜ አራት

**ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍች በቃል ስጡ።**

1. አስፈሪ
2. ተልዕኮ
3. ስል
4. ገሽልጠው
5. ብልህነት
6. ሰለባ
7. ዱር
8. አናሳ
9. ማዘናጋት
10. መጋጥ

## ክፍለጊዜ አምስት

**ተግባር አንድ**

በቡድናችሁ በመሆን ስጋ በልና ሳር በል የሆኑትን እንስሳት በመለየት ስለአካላቸው እና ስለባህሪያቸው ተወያይታችሁ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍሉ ተማሪዎች አስረዱ።



ክፍለጊዜ ስድስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ክፍል የመናገር ክሂላችሁን ለማዳበር የሚያስችሏችሁ የተለያዩ ተግባሮችና መልመጃዎች ቀርበውላችኋል። ስለዚህ በትዕዛዞቹ መሰረት ስሩ።

### ተግባር ሁለት

1. በቡድናችሁ በመሆን ከላይ በምስሉ የምትመለከቷቸው እንስሳት ስማቸውን፣ የሰውነት መጠናቸውን፣ ድርጊታቸውን

እና ባህሪያቸውን በተመለከተ ተወያይታችሁ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ተማሪዎች በቃል አቅርቡ።

2. እንስሳቱ የሚያሰሙትን ድምጽ አስመስላችሁ ለጓደኞቻችሁ አሰሙ።

**መልመጃ ሁለት**

**ቀጥሎ ያሉትን እንስሳት ስጋ በል ወይም ሳር በል በማለት መድባችሁ ማብራሪያ ስጡ።**

| | | |
|---|---|---|
| አነር | ጅብ | ጉሬዛ |
| ሽለምጥማጥ | አጋዘን | አንበሳ |
| ድኩላ | ቀጭኔ | ጦጣ |
| ዝንጀሮ | ጥርኝ | ነብር |

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

**በዚህ ትምህርት ክፍል “የዱር እንስሳት” በሚል ርዕስ ምንባብ እና መልመጃ ቀርቦላችኋል። በመሆኑም መልመጃዎቹን በትዕዛዙ መሰረት ስሩ።**

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

1. የዱር እንስሳት የሚጠበቁበት ስፍራ ምን ይባላል?
2. የዱር እንስሳት ለምን ይጠቅማሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?
3. በሀገራችን ብርቅዬ እንስሳት የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?

## የዱር እንስሳት

በሀገራችን ካሉት የዱር እንስሳት አንበሳ፣ ነብር፣ ቀበሮ፣ ጅብ ወዘተ... በስተቀር ሌሎች በርከት ያሉ ልዩ ልዩ ዓይነት የዱር እንስሳት እንዳሉ ለብዙ ሰዎች ግልጽ አይደለም። በሰሜን ምሥራቅ የሚኖረው ሕዝብ በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙትን እንደ ኒያላና ብሆር ያሉት እንስሳት ምን እንደሚመስሉ አያውቅም። እንዲሁም በምሥራቅና ደቡብ ያሉት ኢትዮጵያውያን በሰሜን የሚገኙትን እንደዋሊያና ጭላዳ ዝንጀሮ ያሉ ብርቅዬ እንስሳት እንዳሉ እምብዛም አይገነዘቡም። ኢትዮጵያ ሰፊ አገር በመሆኗ ከአንዱ ክልል ወደሌላው መሄድ ቀላል አይደለም። ለዚህ ነው በአንዱ ክልል ያለውን የዱር እንስሳ ሀብት የሌላው ክልል ሕዝብ ማየትና ማወቅ የሚሳነው።

ብዙ ሰዎች ብርቅዬ የዱር እንስሳት በተለያየ አካባቢ እንደሚገኙ በውል አያውቁም። ለምሳሌ በሰሜን ተራራ አካባቢ የሚኖር ሕዝብ ዋልያ የሚባለውን የዱር ፍየል በየጊዜው ስለሚያየው ይህ እንስሳ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኝ ይመስለዋል። እንዲሁም ከኢትዮጵያ በስተቀር በሌላ አገር አለመኖሩን ቢነግሩት ማመን ያስቸግረዋል። ስለሆነም ይህ እንስሳ ለኛ ምን ያህል ብርቅ እንደሆነ መገመት ይሳነዋል። እያንዳንዱን የዱር እንስሳ ዘር እየተንከባከብን በመጠበቅ ፈንታ እያደንን እንገላለን። ይህም ባይሆን እያባረርን ከድንበራችን ወጥተው ወደሌላ አገር እንዲሰደዱ እናደርጋለን።

በዚህ ሁኔታ በሀገራችን የእንስሳቱ ዝርያ ቀጣይነት እንዳይኖራቸው የምናደርገው ስለእንሰሳቱ ያለን እውቀት በማነሱ ምክንያት ነው።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. በአገራችን የሚገኙ የዱር እንስሳት ______፣ ______፣ _____፣ ______፣ ______፣ ______፣ ______፣ ______፣______፣ ______ ወዘተ. ናቸው።
2. በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ የዱር እንስሳት______፣______፣ ______፣______ እና ______ናቸው።

በቀድሞ ጊዜ ሰዎች ለራሳቸው ዝና እንጂ ለዱር እንስሳት የሚያደርጉት እንክብካቤ አነስተኛ ነበር ። አንበሳ፣ ነብር፣ ዝሆንና አውራሪስ መግደል ምን ያህል ጀብድ ይጨምር እንደነበር የሚነገርላቸው ገድልና የሚገጠምላቸው ግጥም ይታወቅ ነበር። አሁን ግን በሌላው አገር ሲሆን እንደምናየው ሕዝቡ እየተማረና እየተራቀቀ ሲሄድ ከመግደል ይልቅ እንስሳው ምን እንደሚመስል፣ ባህርይው እንዴት እንደሆነና የአኗኗሩን ሁኔታ መመራመርና መገንዘብ እየመረጠ መጥቷል። ስለዚህም በጥይት ከመምታት ይልቅ በካሜራ ፎቶግራፍ ማንሳት ጀምሯል። አለዚያም ጫካ ለጫካ እየተሽሎከለከ የአራዊቱን ግላዊ ስሜትና ማሕበራዊ ኑሮ የመሳሰሉትንም በመገንዘብ ሕሊናውን ለማርካት እየተጠቀመባቸው ነው። ዱር ሄዶ እንስሳቱን ማየት ከሚሰጠውም ደስታ የበለጠ

የእንስሳው ስም ምን እንደሆነ ማወቅና ከሌሎች የሚለይባቸውን ምልክቶች ማወቅ ያስችላል።

የአገራችን ሰዎች ስለዱር እንስሳትና ስለሚያስፈልጋቸው እንክብካቤ ያላቸው ዕውቀት አነስተኛ ነው። የዱር እንስሳት የትኞቹ እንደሆኑ፣ አንዱ ከሌላው የሚለየው እንዴት እንደሆነና ስሜቱና ባህርይው ምን እንደሚመስል ብናውቅ መጀመሪያ ለተፈጥሮ ያለን በጎ ስሜት ይጨምራል። በዚህም ላይ ደግሞ የዱር እንስሳቱ ዝርያ ቀጣይ እንዲሆን በሚደረገው ጥንቃቄ ሁሉ በሙሉ ፈቃደኝነት ለመሳተፍ ያስችለናል። የዱር እንስሳት ደህንነት የሚጠበቀው በመንግስት ሕግ ብቻ ሳይሆን በህዝቡም በጎ ፈቃድ ጭምር ነው።

(ፍሰሃ ሃይለመስቀል (ዶ/ር) ታላላቅ የዱር እንስሳት በኢትዮጵያ፣ 2011 ለትምህርቱ እንዲሆን ተደርጎ የተወሰደ)

**ክፍለጊዜ ስምንት**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሶስት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በተሟላ ዓረፍተነገር በጽሁፍ መልሱ።**

1. የዱር እንስሳትን አስመልክቶ ለብዙ ሰዎች ግልጽ አይደለም የተባለው ምንድነው?
2. በሰሜኑ አገራችን ያሉትን የዱር አራዊትን በሌሎች ክልሎች ያሉ ነዋሪዎች የማያውቁት ለምን ይመስላችኋል?

3. ሕዝቡ ለዱር እንስሳት ያለው ግንዛቤ ተቀይሮ ከማደን ሀሳቡን የቀየረው ከምን የተነሳ ነው?
4. “ሰዎች ለራሳቸው ዝና እንጂ…” ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
5. “በሌላ አገር አለመኖሩን ቢነግሩት…” የተባለው ማነው?
6. “የዱር እንስሳቱ ዝርያ ቀጣይ እንዲሆን…” ሲል ምን ማለቱ ነው?

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

**ለ. በምንባቡ መሰረት ቀጥሎ የቀረቡት ሀሳቦች ትክክል ከሆኑ ”እውነት ”ትክክል ካልሆኑ ”ሐሰት ” በማለት በምክንያት አስደግፋችሁ በጽሑፍ መልሱ።**

1. ብዙዎች ስለዱር እንስሳት ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ ነው።
2. የዱር ፍየል ወይም ዋልያ በሰሜን ተራራ አካባቢ በሚኖር ሕዝብ ዘንድ ይበልጥ ይታወቃል።
3. በጣም ከታወቁት እንስሳት ውጭ በርከት ያሉ ልዩ ልዩ እንስሳት በአገራችን እንደሚገኙ ብዙ ሰዎች አያውቁም።
4. የአገራችን የዱር እንስሳትን ከነባህሪያቸው ማወቅ ለተፈጥሮ ያለን በጎ ስሜት ላይ ምንም አይጨምርም።
5. እንደአንበሳ ያሉትን የዱር እንስሳት መግደል ድሮ ለገዳዮቹ ሙገሳ ያስገኝ ነበር።

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት ክፍል አወዳዳሪና አነጻጻሪ አንቀጽ ሊያጽፋችሁ የሚያስችል ተግባር ቀርቧል። በመሆኑም በትእዛዙ መሰረት ስሩ።

ክፍለጊዜ አስር

**ተግባር ሶስት**

**ማስታወሻ**

**ማወዳደር እና ማነጻጸር፡** ስታወዳድሩ በሁለት ነገሮች መካከል ያሉትን ተመሳሳይ ነጥቦች እያነሳችሁ ትጽፋላችሁ። ስታነጻጽሩ ደግሞ ልዩነታቸው ላይ ታተኩራላችሁ።

**ሀ. ቀጥሎ በቀረቡት መነሻ ሀሳቦች ታግዛችሁ ከ25 ቃላት ባላነሰ አወዳዳሪ አንቀጽ ጻፉ።**

አንበሳና ነብር ስጋ በል እንስሳት በመባል ይታወቃሉ። ሁለቱም...

**ለ. ቀጥሎ በቀረቡት መነሻ ሀሳቦች ታግዛችሁ ከ25 ቃላት ባላነሰ አነጻጻሪ አንቀጽ ጻፉ።**

አጋዘን ሳር በል ሲሆን፣ ነብር ግን ስጋ በል የዱር እንስሳ ነው። አጋዘን... ነብር...

ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በቀጣይ ለቃላት ተመሳሳይ ፍች እንድትሰጡ የሚያግዙ መልመጃዎች ቀርበዋል። በመሆኑም በትዕዛዞቹ መሰረት ስሩ።

## መልመጃ አራት

ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከሰጣችሁ በኋላ ዓረፍተነገር መስርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ። ቃላቱ ቅርጻቸውን ሊቀይሩ ይችላሉ።


ምሳሌ፡

አደፈጠ፡ ሥጋ በል እንስሳት ሰለባቸውን አድፍጠው በመያዝ ይታወቃሉ።

1. ብርቅዬ
2. መሰደድ
3. ቅርስ
4. ገድል
5. ጀብድ

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

ለ. ከዚህ በታች የቀረበውን የቃላት ጽንሰ ሀሳብ ንድፍ ካሟላችሁ በኋላ በንድፉ መሰረት ዓረፍተነገር መስርቱ።




ምሳሌ

ቀበሮ ውሻ መሳይ የዱር እንስሳ ነው።

ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

ሐ. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከሰጣችሁ በኋላ ዓረፍተነገሮችን መስርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ። ቃላቱ ቅርጻቸውን ሊቀይሩ ይችላሉ።

ምሳሌ፡

አደፈጠ፡ ሥጋ-በል እንስሳት ሰለባቸውን **አድፍጠው** በመያዝ ይታወቃሉ።

| | |
|---|---|
| ብርቅዬ | ጀብድ |
| መሰደድ | አራዊት |
| ዝርያ | ዱር |
| ገድል | መራቀቅ |
| መሸሎክሎክ | |

ክፍለጊዜ አስራ አራት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ክፍል ቃላትን በምዕላድ እንድትከፋፍሉ፣ በመስራች ምዕላዶች አዳዲስ ቃላትን እንድትመሰርቱ፣ ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶችን እንድትለዩ የሚረዱችሁ መልመጃዎች ቀርበዋል። ስለዚህ በትዕዛዞቹ መሰረት በትኩረት ስሩ።

### መልመጃ አምስት

ቀጥሎ ያሉትን ቃላት በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ቃላትን በምዕላድ ከፋፍላችሁ አሳዩ።

ምሳሌ፡ አውሬዎቹን - አውሬ- ኦች- ኡ- ን

1.በጊዜያቸው

2. አንበሳዎቹ

3. ድንበራችን

4. በጨዋታው

5. አለመኖሩን

**ክፍለጊዜ አስራ አምስት**

## መልመጃ ስድስት

**ሀ. ቀጥሎ በቀረቡት ምሳሌዎች መሰረት ቃላትን መስርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

| ቃል | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ገደለ | ገዳይ | መግደል | አገዳደል |
| 2 | ዘፈነ | | | |
| 3 | ፈለጠ | | | |
| 4 | ገመተ | | | |

**ክፍለጊዜ አስራ ስድስት**

**ለ. ቀጥሎ በቀረቡት ምሳሌዎች መሰረት ቃላትን አራብታችሁ ለመምህራች አሳዩ።**

| | |
|---|---|
| ምሳሌ፡ ልጅ | ልጆች፣ ልጅትዋ፣ ልጁ፣ ልጄ፣ ልጆችን፣ ልጁን |

1. ድመት
2. በግ
3. በቅሎ

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### ማስታወሻ

**ተሻጋሪና የማይሻገሩ ግሶች**

**ተሻጋሪ** ግስ በዓረፍተነገር ደረጃ ሲዋቀር ድርጊት የሚያርፍበት ስም ወይም ተሳቢ ስማዊ ሀረግን የሚወስድ ግስ ነው።

**ምሳሌ**

አልማዝ ሽንኩርት ተከለች።

አልማዝ ወንድሟን ሽንኩርት አስተከለች።

**የማይሻገሩ ግሶች** ደግሞ በዓረፍተነገር ደረጃ ድርጊት በባለቤቱ ላይ የሚፈጸም መሆኑን የሚያሳይ ወይም ድርጊቱ ወደሌላ አካል ያልተሻገረ መሆኑን የሚያሳይ የግስ ዓይነት ነው።

**ምሳሌ**

ሀ. ልጁ ሄደ።

ለ. ፀሐይ ወጣች።

መልመጃ ሰባት

ሀ. ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ተሻጋሪ እና የማይሻገሩ ግሶችን ለዩ።

1. ልጁ ሞተ።
2. ሁሉም ሰው ሄዷል።
3. ዘበኛው ሌባውን ገደለ።
4. ትምህርትቤታችን ውድድር ያደርጋል፡፧
5. አባቴ ሰዓት ሰጠኝ።
6. ጨረቃዋ ወጣች።
7. ኃላፊው መኪና ገዛ።
8. አልማዝ ችግኝ ተከለች።
9. ሠራተኛው ብሔራዊ በዓሉን አከበረ።
10. መሬቱ ለማ።

ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

ለ. ከላይ በተሰጠው ማስታወሻ መሰረት በራሳችሁ ተሻጋሪ እና የማይሻገሩ ግሶችን የያዙ አስር አስር ዐረፍተነገሮችን መስርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ለምሳሌ፡ አዳኙ አንበሳ ገደለ። (ተሻጋሪ)

አንበሳው ተገደለ። (ኢ-ተሻጋሪ)

# ምዕራፍ ዘጠኝ፡ ባህላዊ ጨዋታዎች

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ስለባህላዊ ውድድሮችና ጨዋታዎች አዳምጣችሁ ምላሽ ትሰጣላችሁ፤
- ስርዓተነጥቦችን እየተረዳችሁ ፍች በሚሰጥ መልኩ ጥቅም ላይ ታውላላችሁ፤
- ውስብስብ የሆኑ ቀለሞችን ታጣምራላችሁ፤
- ደብዳቤ ትጽፋላችሁ፤
- የአሁን ጊዜን ለይታችሁ ትጠቀማላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት “የገበጣ ጨዋታ” በሚል ርዕስ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ በትኩረት ኣዳምጡ። በመቀጠል የቀረቡትን የተለያዩ ተግባሮችንና መልመጃዎችን ስሩ።

# የገበጣ ጨዋታ



## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ከላይ ከተመለከታችሁት ስዕል ምን ተረዳችሁ?
2. ስለገበጣ ጨዋታ የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

**መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ እየተከታተላችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሳቸውን በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ አስፍሩ።**

1. የገበጣ ጨዋታ ብዙጊዜ በ__________፣ __________ እና በ ______ ሰዎች መካከል ይከናወናል።
2. ለገበጣ ጨዋታ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች __________፣ __________ እና______ ናቸው።

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ጽሑፍ መሰረት በቃል መልሱ።**

1. ገበጣ ስንት የመጫወቻ ጉድጓዶች አሉት ?
2. የተበሉ ጶቃዎች ወይም ጠጠሮች የሚቀመጥበት ጉድጓድ ምን ይባላል?
3. የገበጣ ጣውላ በማይኖርበት አጋጣሚ ጨዋታውን ለመጫወት ምን ይደረጋል?
4. የገበጣን ጨዋታ በየትም ስፍራ መጫወት የሚቻለው ለምንድን ነው?
5. የተለየ የአቆጣጠር ችሎታና ብልሃት ያስፈልጋል። በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ፍች ምንድን ነው?

**ለ. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ከዚህ በታች የቀረቡት ሀሳቦች ትክክል ከሆኑ “እውነት” ትክክል ካልሆኑ “ሐሰት” በማለት በቃል መልሱ።**

1. የገበጣ ጨዋታን ለማሸነፍ የተለየ የአቆጣጠር ችሎታና ብልሃት ያስፈልጋል።
2. የገበጣ ጨዋታ የእድሜ ባለፀጎች ብቻ የሚጫወቱት ነው።
3. የገበጣ ጨዋታ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ ባህላዊ ጨዋታ ነው።
4. በአንዳንድ ቤተሰቦች ወጣት ወንድ ሲያገባ አባቱ ከሙሽሪት ጋር እንዲጫወት የገበጣ መጫወቻ ጣውላ ያዘጋጁለታል።
5. የገበጣ መጫወቻ ጣውላ ለመያዝ አስቸጋሪ ስለሆነ ከቦታ ቦታ ማዛወር አይቻልም።

ክፍለጊዜ ሶስት

ሐ. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍች በቃል ስጡ።

1. ዶቃ
2. ማንጠልጠል
3. መልቀም
4. ቀጣይ
5. ጉድጓድ
6. ላላ
7. ማሸነፍ
8. ማንቀሳቀስ
9. ስፍራ
10. በርካታ

ክፍለጊዜ አራት

ተግባር አንድ

ሀ. በቡድናችሁ በመሆን ጠጠሮችንና ጉደጓዶችን አዘጋጅታችሁ የገበጣ ጨዋታ በመጫወት አሳዩ።

ለ. እንደገበጣ ጨዋታ በአካባቢያችሁ ሰዎች የሚጫወቷቸውን ባህላዊ የጨዋታ አይነቶች በመጠየቅ እንዴት እንደሚጫወቱና የጨዋታው ህግ ምን እንደሆነ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

ክፍለጊዜ አምስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ክፍል በተለያዩ ጉዳዮች ላይ እንድትናገሩ የሚያስችሏችሁ ተግባሮች ቀርበዋል። በየተግባሮቹ ስር በሚሰጧችሁ ትእዛዞች መሰረት ስሩ።

**ተግባር ሁለት**

ሀ. ቀጥሎ የቀረቡት ባህላዊ ጨዋታዎች የሚመሩባቸውን ሕጎች በተመለከተ በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍሉ ተማሪዎች ማብራሪያ ስጡ።

1. የፈረስ ግልቢያ
2. ትግል
3. ውሃ ዋና
4. ሩጫ

**ክፍለጊዜ ስድስት**

ለ. ከዚህ በመቀጠል ከቀረቡት ጨዋታዎች መካከል አንዱን በመምረጥ በቡድን ሆናችሁ መምህራችሁ በሚመሯችሁ መሰረት ተጫወቱ።


- ድብብቆሽ
- የሩጫ ውድድር
- መሃረቤን ያያችሁ
- የዱላ ወይም የኳስ ቅብብሎሽ


**ክፍለጊዜ ሰባት**

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

በመቀጠል የማንበብ ክሂላችሁን እንድታዳብሩ የሚረዳችሁ ምንባብ ቀርቧል። ምንባቡን መሠረት አድርገው የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዞቻው መሠረት ስሩ።

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች





1. ከላይ ከተመለከታችኋቸው ስዕሎች የተረዳችሁትን ተናገሩ።
2. የልጆች ጨዋታ የሚለው ስያሜ ከምን የተገኘ ይመስላችኋል?
3. ልጆች ከሚጫወቷቸው ጨዋታዎች ምን መማር ይችላሉ ብላችሁ ታስባላችሁ?

## የልጆች ጨዋታ

ልጆች በየዕድሜ ደረጃቸው የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ። በቤታቸው፣ በሰፈራቸው፣ በትምህርትቤታቸው እንዲሁም ከብት በሚያግዱባቸው ቦታዎች ይጫወታሉ። ይህንንም የሚያደርጉት

በሚፈጥሯቸው አጋጣሚዎች እየተሰባሰቡ እንደየባህላቸው በተለያዩ አቀራረቦች ነው። ብዙዎቹ የልጆች ጨዋታዎች በግጥምና በዜማ የሚቀርቡ ሲሆኑ እንደስነቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ በመተላለፍ የሚነገሩ ናቸው። ጨዋታዎቹ የየራሳቸው ደንብና ስርዓት ያላቸውና ልጆቹ ራሳቸው በሚፈጥሯቸው፣ በወላጆቻቸው፣ በቤተሰብና ጎረቤት በሚገኙ አዋቂዎች፣ እንዲሁም መምህሮቻቸው ልጆቹን ለማጫወት በሚያመቻቸው አጋጣሚዎች ላይ የሚከወኑ ናቸው። አንዳንዶቹ ጨዋታዎች ወንዶችና ሴቶች ልጆች በጋራ የሚጫወቷቸው ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ለየብቻቸው የሚጫወቷቸው ናቸው።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የልጆች ጨዋታ የሚከናወነው የት የት ነው?
2. የልጆች ጨዋታዎች የሚከወኑት በ__________፣ በ__________፣ __________ እና በ ____________ አመቻችነት ነው።

የልጆች ጨዋታ ክዋኔ እንደባህሉ፣ እንደጨዋታው ዓይነትና እንደልጆቹ እድሜ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። ጫወታዎቹም በአብዛኛው በአካል እንቅስቃሴ የታጀቡ ናቸው። ልጆች ብዙውን ጊዜ የሚጫወቱት በመዝለል፣ በመሮጥ፣ በመቀመጥ፣ በመነሳት፣ እጅና እግርን በመዘርጋት፣ እጅ ለእጅ በመያያዝ፣ ክብ ሰርተው በመቆም ወይም በመቀመጥ በመሳሰሉት እንቅስቃሴዎች ነው።

በጨዋታው ጊዜ የሚሏቸውም ዜማዎች ከነዚሁ እንቅስቃሴዎች ጋር አብረው የሚሄዱ ናቸው፡፡

በልጆች ጨዋታ ጊዜ የሚዜሙት ግጥሞች አብዛኛዎቹ አጠር አጠር ያሉ ናቸው፡፡ ሲከወኑም ፍጥነት ይታይባቸዋል፡፡ ቃላትን፣ ሐረጋትንና አረፍተነገሮችን የሚደጋግሙ ሆነው ይታያሉ፡፡ ጥቂቶቹ ደግሞ ረዘም ረዘም ያሉና የመተረክ ባህሪ ያላቸው ናቸው፡፡ ከአጫጭሮቹ "መሐረቤን ያያችሁ"፣ "ጉልበቴ በርታ በርታ"፣ "ድምቡሼ ገላ" የተሰኙት የታወቁ ናቸው፡፡ ረዘም ካሉት ደግሞ "መሶበ ወርቂ" እና "እቴ እሜቴ" የተሰኙት ይጠቀሳሉ፡፡

(ዘሪሁን አስፋው፣ የስነጽሁፍ መሰረታውያን ላይ ተቀንጭቦ የተወሰደ)

ክፍለጊዜ ስምንት

## አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡**

1. ለልጆች ጨዋታ መነሻ የሚሆኑ ሰበቦች ምን ምን ናቸው?
2. የልጆች ጨዋታ ከትውልድ ወደትውልድ የሚተላለፈው እንዴት ነው?
3. አብዛኛው የልጆች ጨዋታ የሚቀርበው በግጥም መልክ መሆኑ ለምን ይመስላችኋል?
4. "የልጆች ጨዋታ በአብዛኛው በአካል እንቅስቃሴ ይታጀባል" የሚለው ሃሳብ የትኞቹን እንቅስቃሴዎች ለመግለጽ ነው?

5. አብዛኛዎቹ በልጆች ጨዋታ ጊዜ የሚዜሙ ግጥሞች ምን ዓይነት ናቸው?

**ለ. በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ሀሳቦች ትክክል ከሆኑ “እውነት” ትክክል ካልሆኑ “ሐሰት” በማለት በጽሐፍ ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያት ስጡ።**

1. በማንኛውም የዕድሜ ደረጃ ያሉ ልጆች በጋራ የሚጫወቷቸው ጨዋታዎች ተመሳሳይ ናቸው።
2. የልጆች ጨዋታዎች የየራሳቸው የመጫወቻ ደንብና ስርዓት አሏቸው።
3. የልጆች ጨዋታዎች የልጆቹ የራሳቸው ፈጠራ ሥራዎች ናቸው።
4. በልጆች ጨዋታ ጊዜ የሚዜሙ ግጥሞች ረጃጅም እና አጫጭር ሊሆኑ ይችላሉ።
5. ብዙውን ጊዜ የልጆች ጨዋታ በገጠር ተዘውትሮ ይከወናል።

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

**ሐ. ከዚህ በታች ከምንባቡ የወጡትን ቃላት ተጠቅማችሁ ዓረፍተነገሮችን በመመስረት ለመምህራችሁ አሳዩ። የቃሉ ቅርጽ ሊቀየር ይችላል።**

**ምሳሌ፡ ደረጃ-** የህፃናት ጨዋታዎች በደረጃ የተለያዩ ናቸው።

| | | |
|---|---|---|
| 1. ተላለፈ | 4. ጎረቤት | 7. ተረከ |
| 2. አገደ | 5. ዜማ | 8. ተሰበሰበ |
| 3. ክዋኔ | 6. ደንብ | 9. ታጀበ |

ክፍለጊዜ አስር

ተግባር ሦስት

መሐረቤን ያያችሁ ስለሚለው የልጆች ጨዋታ ከጽሁፍ በማንበብ ወይም ከሚያውቁ ሰዎች በመጠየቅ እንዴት እንደሚከወን ጽፋችሁ ከመጣችሁ በኋላ በቡድን በመሆን አደራጅታችሁ በተወካዮቻችሁ በኩል ዘገባ አቅርቡ።

ክፍለጊዜአስራ አንድ

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት ክፍል ደብዳቤ ለመጻፍ የሚያስችላችሁ ማስታወሻ እና ተግባሮች ቀርበዋል። በመሆኑም በትዕዛዙ መሰረት ስሩ።

**ማስታወሻ**

የሰላምታ ደብዳቤ ለመጻፍ ቀጥሎ ያለውን ሂደት ተከተሉ።

1. የተጻፈበት ቀን
2. የተቀባይ ስምና አድራሻ
3. ፖስታ ሣጥን ቁጥር
4. ከተማ ወይም ሰፈር
5. ሰላምታና አነሳሽ ምክንያት በዝርዝር
6. ተጨማሪ ምክንያት (መልዕክት) ካለንና የስንብት ምኞት የላኪው ስምና ፊርማ

**የሰላምታ ደብዳቤ ናሙና**

ሜቲ ገመቹ

የላኪ አድራሻ
- ዱከም አንደኛ ደረጃ ት/ቤት
- የመ.ሳ.ቁ. 1127
- ዱከም
- 12/12/2013

ለፍራኦል ገመቹ
ወለጋ ዩኒቨርሲቲ
የመ.ሳ.ቁ. 1197
ነቀምቴ

የተቀባይ አድራሻ

**መግቢያ፡**ውድ ወንድሜ ፍራኦል እንደምን አለህ? እኔ ደህና ነኝ።

**ሀተታ፡** ውድ ወንድሜ ባለፈው ጊዜ የላክልኝ ብር ደርሶኛል።
በጣም አመሰግናለሁ። እንደደረሰኝ ወዲያውኑ ለላክልኝ
አላማ አውዬዋለሁ። ምንም አላባከንኩም።

**መደምደሚያ፡** በል ወንድሜ በሰላም ለመገናኘት ያብቃን።

እህትህ ሜቲ

ፊርማ

**ተግባር አራት**

**ከላይ የቀረበላችሁን ናሙና ደብዳቤ መሰረት አድርጋችሁ ለቅርብ ጓደኛችሁ አጠር ያለ ደብዳቤ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ።**

**ክፍለጊዜ አስራ ሁለት**

**"የልጆች ጨዋታ" የሚለውን ምንባብ ዋና ዋና ሀሳቦች አሳጥራችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

- ስለ ተጻፈበት ጉዳይ
- ለማስረዳት ያሰበውን ሃሳብና
- የቀረቡትን ምሳሌዎች አካትቱ።

**ክፍለጊዜ አስራ ሶስት**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

**በዚህ ትምህርት ክፍል ተዘውታሪ ቃላትን ተዘውታሪ ካልሆኑ ቃላት መለየት እና ቃላትን መመስረት የሚያስችሏችሁ መልመጃዎች ቀርበውላችኋል ። በትዕዛዞቹ መሰረት ስሩ።**

### መልመጃ ሶስት

**ሀ. ቀጥሎ ከቀረበት ቃላት ተዘውታሪ የሆኑና ያልሆኑትን ለዩ።**

1. ሰፈር
2. ከብት
3. ቁርስ
4. ክዋኔ
5. ትርክት
6. እርቦ
7. ምግብ
8. እንዝርት
9. ዘፈን
10. እንቅልፍ

**ለ. ከዚህ በመቀጠል የቀረቡትን ቃላት በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ስሩ።**

ምሳሌ፡ አጀበ ብሎ አጃቢ ካለ፣ ጀመረ ብሎ ምን ይላል?

መልስ፡ ጀማሪ

1. ጋለበ
2. አከመ
3. ጻፈ
4. ወረሰ
5. ጨረሰ
6. ዘነጠ
7. አረካ
8. ጠቀመ
9. ፈጠረ

ክፍለጊዜ አስራ አራት

**ሐ. ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ መርጣችሁ በክፍት ቦታዎች በማስገባት አንቀጹን አሟሉ።**

| አገናኝታ | ሳያጠፋ | ለመግዛት | ፈንታ | ሂዶ | ዕውቀት |
|---|---|---|---|---|---|

ትምህርትቤት———የሚገበይባት ገበያ ናት ማለት ይቻላል። ለምሳሌ አንድ ሰው ፈረስ፣ ጥጥ እና ጤፍ ——— ቢፈልግ፣ ፈረስ ለመግዛት ወደ ደጋ፣ ጥጥ ለመግዛት ወደቆላ፣ ጤፍ ለመግዛት ወደወይና ደጋ በመንከራተት——— በቀጥታ ወደገበያ ——— ሳይንገላታና ብዙ ጊዜ——— የፈለገውን ሁሉ ከአንድ ቦታ በአንድ ጊዜ ገዝቶ ወደቤቱ ይመለሳል። እንዲሁም ትምህርት ቤት ትምህርት የሚሰጡትንና ትምህርት የሚፈልጉትን አንድ ላይ——— ተማሪዎች ትምህርት በተወሰነ ጊዜ ከአንድ ቦታ እንዲያገኙ ታደርጋለች።

ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

**በዚህ ትምህርት ክፍል በዓረፍተነገር ውስጥ የአሁን ጊዜን የሚያሳይ ማስታወሻ እና መልመጃዎች ቀርበውላችኋል። በመሆኑም በተሰጣችሁ ትዕዛዝ መሰረት መልመጃዎቹን ስሩ።**

**ማስታወሻ**

**የአሁን ጊዜ**

ጊዜ የሚባለው ድርጊት የተፈጸመበት ወይም የሚፈጸምበት ወቅት ነው። ድርጊቱ በንግግሩ ወቅት ተፈጽሞ ያበቃ ከሆነ ጊዜው ኃላፊ ይሆናል። ድርጊቱ በንግግሩ ወቅት እየተፈጸመ ያለ ከሆነ ጊዜው የአሁን ጊዜ ይሆናል።

ምሳሌ፡

1. አበበ ቡና ጠጣ። (ኃላፊ ጊዜ)
2. አበበ ቡና እየጠጣ ነው። (የአሁን ጊዜ)

## መልመጃ አራት

**ሀ. የሚከተሉትን ጅምር ዓረፍተነገሮች የአሁን ጊዜን በሚጠቁሙ ሀረጎች አሟሉ።**

1. ገነሞ የክፍል ፈተናውን __________________።
2. ዘምዘም እንጀራ __________________።
3. ሂሩት አልጋ __________________።
4. ቅዝቃዜው __________________።
5. ገበሬው ማሳውን __________________።
6. ፈተና ስለደረሰብኝ __________________።
7. የአካባቢ ጥበቃ ላይ __________________።
8. ሙቀቱ ስለበረታ __________________።
9. በርጩማዬ ላይ __________________።

## ክፍለ ጊዜ አስራ ስድስት

**ለ. ከዚህ በታች በሃላፊ ጊዜ የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች ወደ የአሁን ጊዜ ቀይሩ።**

1. አበራ ልጁን አስተማረ።
2. ዋቆ ግብር ገበረ።
3. ሣራ ሊጥ አቦካች።
4. ልጆቹ ብሔራዊ መዝሙር ዘመሩ።
5. አዛውንቱ በችግኝ ተከላው ላይ ተሳተፉ።
6. ሕጻኑ የእናቱን ጡት ጠባ።
7. ጥናቱን ጨርሶ እረፍት ወሰደ።
8. ዝናቡ ዘነበ ።
9. ልጁ መዝሙር ዘመረ።
10. ቅዝቃዜ ስላለ ኮት ደረብኩ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

**ሐ. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች የአሁን ጊዜ ወይም ሀላፊ ጊዜ በማለት ለይታችሁ ጻፉ ።**

1. የኮሮና ቫይረስ ስርጭት በጣም እየተባባሰ ነው።
2. እ.ኤ.አ. በ2019 በርካታ የሀገራችን ሴት አትሌቶች የሜዳሊያ ባለቤት ሆነዋል።
3. ለአባይ ግድብ ስራ መጠናቀቅ በርካታ የአገራችን ህዝቦች ድርሻቸውን እየተወጡ ነው።
4. ነጋዴዎች የሚጠበቅባቸውን ግብር እየከፈሉ አይደለም ።

5. ኤችአይቪ/ኤድስ የበርካታ ዜጎችን ህይወት ቀጥፏል።

**ክፍለጊዜ አስራ ስምንት**

**መ. የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም የአሁን ጊዜን የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮች መስርቱ።**

**ምሳሌ፡ በላ፡ አራርሳ ምሳውን እየበላ ነው።**

1. መጣ
2. ሰራ
3. መከረ
4. ዘነበ
5. አገዘ

6. አነበበ
7. ፎከረ
9. አረሰ
10. ተራመደ

# ምዕራፍ አስር፡ ስነቃል

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ስነቃልን አዳምጣችሁ ምላሽ ትሰጣላችሁ።
- ስለራሳችሁ ትገልጻላችሁ።
- የዝነኞችን ታሪክ አንብባችሁ ምላሽ ትሰጣላችሁ።
- ግለታሪካችሁን ትጽፋላችሁ።
- የሥነጽሁፍ አላባውያንን ለይታችሁ ትናገራላችሁ።

**ክፍለጊዜ አንድ**

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በዚህ ትምህርት ክፍል ስለስነቃል የሚያወሳ የማዳመጥ ግብዓት፣ መልመጃዎችና ተግባሮች ስለቀረቡ በትዕዛዞቹ መሰረት በትኩረት ስሩ።**

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. የምታውቋቸውን የልጆች ጫወታ፣ የዓውደዓመት እና የስራ ላይ ግጥሞችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ?
2. ከላይ ያስታወሳችኋቸው ግጥሞች ጠቅለል ተደርገው ሲጠሩ ምን ይባላሉ?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የስነቃል ዓይነቶች _____፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____እና ______ ናቸው።
2. የስነቃል አገልግሎቶች ምን ምን ናቸው?
3. ስነቃል የሚተላለፈው እንዴት ነው?

**ክፍለጊዜ ሁለት**

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት ጽሁፍ መሰረት በቃል መልሱ።**

1. የስነቃል ዓይነቶች በምን በምን መልክ ተቀናጅተው ይቀርባሉ?
2. "ስነቃል ዘመን ተሻጋሪ ነው" ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. ስነቃል ለሕብረተሰቡ ምን ምን ጠቀሜታ ይሰጣል?
4. የታሪክ ተመራማሪዎች በስነቃል ላይ ትኩረት የሚያደርጉት ለምን ይመስላችኋል?
5. "የስነቃል ቅርሶች የማሕበረሰቡን የኑሮ ዘይቤ ይገልጻሉ።" ሲል ምን ማለት ነው?

**ክፍለጊዜ ሶስት**

**ለ. በአዳመጣችሁት ጽሁፍ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከቀረቡ አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. በስነቃል ዓይነት ውስጥ የማይጠቀሰው የቱ ነው?

   ሀ. ቀረርቶ ሐ. ልቦለድ

   ለ. ባህላዊ ዘፈን መ. ተረት

2. ስነቃሎች በሕዝብ ኑሮና አኗኗር ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡባቸው ቅርጾች የትኞቹ ናቸው?

   ሀ. ዘፈን ሐ. መዝሙር

   ለ. ቀረርቶ መ. ሁሉም መልስ ነው።

3. "ስነቃል የባህልና የታሪክ ቅርስ ነው" የተባለው ለምንድነው?

   ሀ. ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ መምጣቱ

   ለ. አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑ

   ሐ. በግጥም መልክ የሚቀርብ መሆኑ

   መ. መልሱ አልተሰጠም

4. የስነቃል አገልግሎት ከሆኑት ውስጥ የማይካተተው———

   ሀ. ክፉና ደጉን ማስገንዘብ ሐ. ማስተማርና ማዝናናት

   ለ. መምከርና መገሰጽ መ. ወንጀለኞችን መቅጣት

5. ከስነቃል መገለጫ ባህርይ አንዱ የሆነው ምንድነው?

   ሀ. እንስሳትን እንደሰው ማናገር መቻሉ

   ለ. በጽሁፍ ብቻ መተላለፉ

   ሐ. የአንድ ሰው የፈጠራ ሥራ መሆኑ

   መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

## ክፍለጊዜ አራት

### ተግባር አንድ

ከሰዎች ወይም ከራዲዮ የሰማችሁትን አንድ ተረት አሳጥራችሁ ለክፍል ተማሪዎች ተናገሩ።

ክፍለጊዜ አምስት

ተግባር ሁለት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ስር የተለያዩ የስነቃል ዓይነቶችን የያዙ መልመጃዎችና ተግባሮች ስለቀረቡ በትዕዛዛቸው መሰረት ስሩ።

ሀ. ቀጥሎ በቀረቡት ሀሳቦች ዙሪያ የተነገሩ ተረቶችን ከሰዎች ጠይቃችሁ ወደክፍል በማምጣት አሳጥራችሁ ለክፍል ተማሪዎች ተናገሩ።

1. ብልህነትን በተመለከተ
2. ሆዳምነትን በተመለከተ
3. አራዊትን በተመለከተ
4. ንጉስነትን በተመከለተ

**ለ. ተማሪዎች ተረት ሲተርቱ አዳምጣችሁ የተረቱን ጭብጥ ለጓደኞቻችሁ በቃል ተናገሩ።**

ክፍለጊዜ ስድስት

**ሐ. ቀጥሎ የቀረቡትን ስነቃሎች ዓይነታቸውን ለዩና በምን ሁኔታ እንደሚነገሩ ግለጹ።**

**ምሳሌ፡** መልካም ምላስ ቁጣን ታበርዳለች።

ዓይነቱ - ምሳሌያዊ አነጋገር

የሚነገርበት ሁኔታ - መልካም ነገር መናገር ሰላም ማውረድ መቻሉን ለማሳሰብ ነው።

1. ዱብ ዱብ ይላል እንደበረዶ
   በልጅነቱ በረሀን ለምዶ።

የማን ቤት ጠፍቶ፣ የማን ሊበጅ
ያውሬ መፈንጫ፣ ይሆናል እንጂ።

2. የጓሮዬ ቡንኝ አብቢልኝ፣
   የጓሮዬ አባሎ አብቢ ቶሎ፣
3. ላሜ ቦራ፣ ላሜ ቦራ
   የልጆቼን ነገር አደራ።
4. አለባብሰው ቢያርሱ፣ ባረም ይመለሱ።
5. የወረወርኩት አንካሴ፣ ተመልሶ በራሴ።

ክፍለጊዜ ሰባት

**ከዚህ በታች የቀረበውን ጅምር ስነቃል አንብባችሁ ከሥር ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

ቀበሮና አንበሳ ባንድ ላይ ይኖሩ ነበር። አንድ ቀን ለአደን ወጡና ትንሽ ድኩላ አገኙ። አንበሳው ደክሞት ስለነበረ ቀበሮዋ ድኩላዋን አርዳ ምግብ ሰርታ እንድትቀሰቅሰው አዟት ጋደም አለ።...

1. ጅምሩ ሀሳብ በየትኛው የስነቃል ዓይነት ይመደባል?
2. የተጀመረውን በየግላችሁ በመሰላችሁ መንገድ ጨርሱና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ። ጓደኞቻችሁ የሚያቀርቡትንም አዳምጣችሁ በሀሳብ አዳብሩ።

ክፍለጊዜ ስምንት

## ትምህርት ሶስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ክፍል “ዝሆንና ዝንጀሮ” በሚል ርዕስ ምንባብ ፣ መልመጃዎችና ተግባሮች ስለቀረቡ በትእዛዞቹ መሰረት በትኩረት ስሩ።



## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

1. ከላይ ከቀረበው ምስል የተረዳችሁትን ለቡድን ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. ተረት ሲተረት ምን ተብሎ ይጀመራል?
3. ከወላጆቻችሁ ወይም ከሌሎች ሰዎች ያዳመጣችኋቸውን ተረቶች ስለምን እንደሚገልጹ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

## ዝሆንና ዝንጀሮ

በአንድ ወቅት ዝንጀሮና ዝሆን ተረዳድተው አንድ ላይ ይኖሩ ነበር። ዝሆኑ ዓይነስውር ሲሆን ዝንጀሮው ደግሞ እግሩ የተቆረጠ ነው። በአንድ ዓመት በተከታታይ በተፈጠረው የዝናብ መጥፋት ድርቅ ተከሰተ። በድርቁም ሰበብ የሚበላ ሣርና ፍራፍሬ እንዲሁም የሚጠጣ ውሃ ጠፋ። ዝናብ አልዘንብ በማለቱ ችግሩ እየተባባሰ ሄዶ ለሕይወታቸው ስጋት ሆነ።

እናም በአንዱ ቀን ዝሆንና ዝንጀሮ ቁጭ ብለው ስለምግብ እና ውሃ ያወጉ ጀመር። ዝሆኑም እንዲህ በማለት ጀመረ። "እኔ ምግብና ውሃ ልናገኝ የምንችልበትን ትክክለኛ ቦታ አውቃለሁ" አለ። ይህንን የሰማ ዝንጀሮ በጣም ከሳቀ በኋላ "አንተ ዓይነስውር፣ እኔ ደግሞ እግረ ቆራጣ ነኝ" አለው። "ስለዚህ እንዴት አድርገን፣ በምንስ ጥበብ ነው እቦታው ላይ የምንደርሰው?" ሲል ጠየቀው።

ዝሆኑም ነገሩን በማቃለል "ችግር የለውም" በማለት ያለውን ሀሳብ አካፈለው። "እርግጥ ነው እንዳልከውም እኔ ማየት አልችልም፤ መራመድ ግን እችላለሁ። አንተ ደግሞ እግርህ ቆራጣ ስለሆነ መራመድ አትችልም፤ ማየት ግን ትችላለህ። ስለዚህ በጀርባዬ አዝዬህ እቦታው ድረስ እወስድሃለሁ።" ዝንጀሮውም በመሄዱ ተስማምቶ "የምንሄድበትን ቦታ ንገረኝ" አለው። ዝሆኑም "የሰሜን ኮከብን አቅጣጫ ተከተል" አለውና ጉዞ ጀመሩ።
በመጀመሪያው ቀን ከተነሱበት ቦታ በጣም ርቀው መሄድ ቢችሉም የተመኙት ቦታ ሊደርሱ አልቻሉም። የሁለተኛና ሶስተኛ ቀን ጉዟቸው አድካሚና አሰልቺ ሆኖ አለቀ። ጉዞ ጀምረው በአራተኛው ቀን ምግብና ውሃ እንደልብ የሚገኝበት መስክ ደረሱ። በቦታው አንድ ኩልል ያለ ውሃ ያለው ወንዝ አለ። በስፍራው ለዝሆኑ ምግብ የሚሆን ለምለም ሣርና ለዝንጀሮው የሚሆኑ የተለያዩ ፍራፍሬዎች አሉ። ጥረታቸው ፍሬ በማፍራቱ ከደስታ የተነሳ ፈነደቁ። እንደፍላጎታቸው እየተመገቡ፣ ከጠራው ውሃም ጎንጨት

እያደረጉ ረሃብ ጥማታቸውን አስታገሱ። ለዚህ ላበቃቸው አምላክም ተራ በተራ እየደጋገሙ ምስጋና አቀረቡ።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ዝሆንና ዝንጀሮ በአራቱ ተከታታይ ቀናት ያከናወኗቸው ተግባሮች ምን ምን ናቸው?
2. በቀጣይ ዝሆንና ዝንጀሮ ምን የሚያጋጥማቸው ይመስላችኋል?

ከዚያም በልተውና ጠጥተው ሆዳቸውን በመሙላት ነፍሳቸውን ካስደሰቱ በኋላ በወንዙ ዳርቻ ባለው መስክ ላይ ተቀመጡ። ዘና ብለውም ባገኙት አጋጣሚ እየተደሰቱ በአግራሞት ማውጋት ጀመሩ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ ዝንጀሮው አንድ መሰረታዊ ጥያቄ ለዝሆኑ እንዲህ በማለት አቀረበ። "አቶ ዝሆን ይኸንን ገነት የመሰለ ቦታ እንዴት ልታውቅ ቻልክ?" አለው። ዝሆኑም በቀረበው ጥያቄ ብዙም ሳይገረም፣ "እድሜ ልኬን አይነስውር አልነበርኩም" አለው። "ይኸንን ቦታ ያየሁት በወጣትነት ዘመኔ ሲሆን የአካባቢው ገጽታ እስካሁንም ከአእምሮዬ አልጠፋም። በዚያን ዘመን በአካባቢው ብዙ ሰው ይኖር እንደነበረና ሰዎቹ ሁልጊዜ ይጣሉ እንደነበር አስታውሳለሁ። እነዚያ ሰዎች አካባቢውን ለቀው ወደሌላ ቦታ ይሰደዳሉ ብዬ አስብ ነበር። ወደዚህም እንድንመጣ የወሰንኩት ለዚህ ነው፤ ትክክልም ነበርኩ" አለው።

(Ethiopian folk tales:- ministry of education: 2013 ለማስተማሪያ እንዲሆን ተተርጉሞ መጠነኛ መሻሻል ተደርጎበት የቀረበ)

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልሱ።**

1. ዝሆኑና ዝንጀሮው በሚኖሩበት ስፍራ ድርቅ ለምን ተከሰተ?
2. ዝሆንና ዝንጀሮው ከድርቁ አደጋ ያመለጡበትን መላ ዝሆኑ እንዴት ሊያገኝ ቻለ?
3. ዝንጀሮው ተስፋ ሊቆርጥ የተቃረበው ለምንድን ነው?
4. ዝሆኑና ዝንጀሮው ምግብና ውሃ እንዴት አገኙ?
5. በምንባቡ በርካታ ዓረፍተነገሮች በትዕምርተጥቅስ ውስጥ ለምን የገቡ ይመስሏችኋል?
6. በመጨረሻው አንቀጽ "እነዚያ..." የሚለው ቃል እነማንን ያመለክታል?

ክፍለጊዜ አስር

**ለ. በምንባቡ መሠረት ቀጥሎ የቀረቡት ሀሳቦች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት በጽሐፍ መልሱ። መልሳችሁንም በምክንያት አስደግፉ።**

1. ዝንጀሮና ዝሆን የተሰደዱበትን ቦታ በልጅነታቸው ጊዜ ያውቁ ነበር።
2. ዝሆኑ አይነስውር የሆነው ከጊዜ በኋላ ነበር።

3. ዝሆኑና ዝንጀሮው የሄዱበት ቦታ ትላልቅ ወንዞችና የጓሮ አትክልት በብዛት ይገኙ ነበር።
4. ዝንጀሮው የሚሄዱበትን ቦታ ዝሆኑን የጠየቀው በልቶና ጠጥቶ ከጠገበ በኋላ ነበር።
5. ዝሆኑና ዝንጀሮው የሄዱበት አካባቢ የነበሩ ነዋሪዎች ከአካባቢያቸው ለቀው ተሰደዋል።

**ተግባር ሶስት**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንደአጠያየቃቸው መልሱ።**

1. በበጎ ጉዳዮች ላይ ሰዎች ተባብረው ቢሰሩ ውጤቱ ምን ሊሆን ይችላል ብላችሁ ትገምታላችሁ?
2. ከዝሆኑና ዝንጀሮው ሕብረት ምን ተማራችሁ?
3. አራዊትን እንደገፀባህርይ (እንደባለታሪክ) መጠቀም ምን ፋይዳ አለው ብላችሁ ታስባላችሁ?

**ክፍለጊዜ አስራ አንድ**

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት ስር እንድትጽፉ የሚያግዟችሁ ተግባሮችና እና መልመጃዎች ስለቀረቡ በትእዛዞቹ መሰረት ጻፉ።

### መልመጃ ሶስት

**ሀ. በምንባቡ መሠረት ቀጥሎ ያሉትን ጅምር ሀሳቦች አሟልታችሁ ጻፉና ደብተራችሁን ተለዋወጣችሁ ተራረሙ።**

1. በድርቁ ሰበብ ________________________________።

2. ዝናብ አልዘንብ በማለቱ ______________________________።
3. በአንዱ ቀን ዝሆንና ዝንጀሮ ቁጭ ብለው_______________።
4. ጉዞ ጀምረው በአራተኛው ቀን___________________________።
5. ጓደኛሚኞቹ እየተመገቡና____________________________።

**ለ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት ተጠቅማችሁ የተሟሉ ዓረፍተነገሮች በመመስረት ለመምህራችሁ አሳዩ።**

**ምሳሌ፡** ድርቅ - ከብቶቹ የተጎዱት በድርቁ ምክንያት ነው።

1. ተከሰተ
2. መስክ
3. ጥበብ
4. አወጋ
5. ተገረሙ
6. አቃለለ
7. አዘለ
8. አቅጣጫ
9. ሠጋ
10. ተሰደደ

**ክፍለጊዜ አስራ ሁለት**

**ሐ. "ዝሆንና ዝንጀሮ" በሚል ያነበባችሁትን ተረት ዋና ዋና ሀሳቦች አሳጥራችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

**ስትጽፉ፡-**

- ታሪኩ ምን እንደሆነ፣
- ገፀባህሪያቱ የትኞቹ እንደሆኑ፣
- ምን ለማስተላለፍ እንደቀረበ ማካተት አለባችሁ።

**ክፍለጊዜ አስራ ሶስት**

**ተግባር አራት**

ቀጥሎ ግለታሪክ ትጽፋላችሁ። በመሆኑም ከዚህ በታች ያለውን ማስታወሻ በደንብ አንብቡ።

**ማስታወሻ**

ግለታሪክ ስትጽፉ ቀጥሎ ያሉትን ነጥቦች ማካተታችሁን አትርሱ።

ሀ. ስማችሁን ከነአባት

ለ. ትውልድ ቦታ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ ልዩ ስሙ…

ሐ. የትውልድ ዘመን፣ ቀንና ዓመተምህረት

መ. የአስተዳደግና የትምህርት ሁኔታ

ሠ. አሁን ያላችሁበት ደረጃ

ከላይ በማስታወሻው የተሰጧችሁን ነጥቦች ሳትረሱ ግለታሪካችሁን አጠር አድርጋችሁ በመጻፍ ለመምራችሁ አሳዩ።

**ክፍለጊዜ አስራ አራት**

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ስር የቃላት ተዋቃሪዎችን እንድትነጥሉ እና እንድታጣምሩ የሚያግዝ መልመጃ ቀርቦላችኋል። በመሆኑም በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ስሩ።

## መልመጃ አራት

ሀ. ቀጥሎ በተሰጡት ምሳሌዎች መሰረት የቀረቡትን ቃላት በመነጠል አሳዩ።

ምሳሌ፡- በጎች—በግ-ኦች

የሰው—የ-ሰው

ቁሳቁስ—ቁስ-ኣ-ቁስ

1. ዛፎች
2. ቅጠላቅጠል
3. በበሬ
4. አንበሳዎች
5. ለመንግስት
6. ሰዎቹ
7. ሌባዎቹ
8. ወታደራዊ
9. በቤታቸው
10. ቤተኛ

**ክፍለጊዜ አስራ አምስት**

ለ. ከዚህ በታች ተነጣጥለው የቀረቡትን ምዕላዶች አጣምሩ።

1. አህያ-ዋ
2. ዘመን-ኣዊ
3. ጎረቤት-ኦች-ኤ
4. በ-መኪና-ው
5. እናት-ኤ
6. ቂል-ኣ-ቂል
7. ወዳጅ-ነት
8. ጥርጣር-ኤ
9. ወርቅ-ኣማ
10. ጠጣ-ኢ-ት

**ክፍለጊዜ አስራ ስድስት**

ሐ. ቀጥሎ ላሉት ቃላት የብዙ ቁጥራቸውን ስጡና ነጣጥላችሁ አሳዩ።

**ምሳሌ፡ ቤት ቤቶች ቤት -ኦች**

1. መኪና
2. ተራራ
3. ካህን
4. እንስሳ
5. ችግኝ
6. ልብስ
7. ፍሬ
8. ጀግና
9. ምግብ
10. ልባም

**ክፍለጊዜ አስራ ሰባት**

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ቀጥተኛ እና ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢዎችን እንድትለዩ የሚያግዛችሁ መልመጃ ስለቀረበላችሁ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ስሩ።

**ማስታወሻ**

**ዓረፍተነገር በውስጡ ባለቤት፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ይይዛል። ተሳቢ በዓረፍተነገር ውስጥ ድርጊት ተቀባይ ሲሆን ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተብሎ ይለያል።**

**ቀጥተኛ ተሳቢ የዓረፍተነገሩን ማሰሪያ አንቀጽ ይዘን "ምን" ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው ምላሽ ነው።**

**ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢ የሚባለው ደግሞ "ለማን" ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው ምላሽ ነው።**

**ምሳሌ፡**

**"ጫላ ለልጁ መኪና ገዛ።" የሚለውን ዓረፍት ነገር ይዘን "ምን ገዛ?" ብለን ብንጠይቅ "መኪና" የሚል መልስ እናገኛለን። በዚህ ዓረፍት ነገር ውስጥ መኪና የሚለው ስም ቀጥተኛ ተሳቢ ነው። "ለማን ተገዛ?" ብለን ስንጠይቅ ደግም "ለልጁ" የሚል መልስ እናገኛለን። ስለዚህ ለልጁ የሚለው ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢ ነው።**

## መልመጃ አምስት

ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት አድርጋችሁ አምስት ቀጥተኛ ተሳቢና አምስት ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢ ስሞች ያሉባቸውን ዓረፍተነገሮች መስርቱ፡፡

ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

## መልመጃ ስድስት

ከላይ በቀረበው ማስታወሻ ላይ ተመስርታችሁ ቀጥሎ ባሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢዎች ለዩ።

1. ዙፋን ለባሏ ሽልማት ሰጠች።
2. አበባ ጡጦ ገዛች።
3. ቢራቱ ለወዳጁ ሎሚ ወረወረ።
4. ዜይነባ ለአባቷ ቤት ሠራች።
5. ዓሊ ለአማቱ ልብሶች ላከ።
6. ኦሊ ለቤቱ ተጠሪ ሆነ።
7. ፋጡማ ለጓደኛዋ ማስታወሻ ላከች።
8. ወታደሩ ለአገሩ ሕይወቱን ገበረ።